ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the Source of the Blue Nile

# ናይል
# THE NILE



ኢ-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4፣ ግንቦት 2007

## ሴቶች በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)

ፈለገ ህይወት ሆስፒታል - አይሞላልሽ ባተሌ?
ጀማል ሙሀመድ (ዶ/ር)
... ገጽ 7

እኛ እንዲህ እንላለን (ሶስት)
አበባው ይርጋ (ዶ/ር)
... ገጽ 7



Ato Dereje Moges, Vice Manager of Amhara Mass Media Agency (AMMA) and Dr Bayile Damtie, President of BDU addressing the public at the official inauguration of BDU's Television program called "Meskote Tibeb"

ሳይቃጠል በቅጠል
... ገጽ 16

ህይወት (አጭር ልቦለድ)... ገጽ 6
ምኞት (አጭር ልቦለድ)... ገጽ 13

IDዬ (ልቦለዳዊ ወግ)
... ገጽ 12



BDU celebrates first inauguration of professorship of Professor Mulugeta Kibret

እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# ናይል

# THE NILE

## Bahir Dar University

### Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

### Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

### Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

**Core Values**

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility

## ናይል ጋዜጣ

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

የአማካሪ ቦርድ አባላት

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
ዶ/ር ጥጋብ በዜ
ዶ/ር እንየው ታደሰ
አቶ በላይነህ ወርቁ
ወ/ሪት እንዳስ ቃሶ
አቶ ፈታሒ በቃሉ
አቶ ብሩክ ከተማ
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

ዋና አዘጋጅ፡-
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

ም/ዋና አዘጋጆች
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

አርታኢዎች
ሂሩት አድማሱ
አብነት ሰለሞን

ግራፊክስና ሌይአውት፡-
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

ዘጋቢዎች፡-
ትዕግስት ዳዊት
አበባ ሐብቱ
ሙሉጎጃም አንዷለም

አምደኞች፡-
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ጀማል ሙሀመድ (ዶ/ር)
አበባው ይርጋ (ዶ/ር)
ሠለሞን ንጉስ
ደስታ ተከስተ
እንዳለካቸው አበበ
መክሊት ጋረደው

ፎቶ አንሺዎች፡-
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ

ትራንስፖርት፡-
ማናለ ኃይሌ

መልእክተኞች፡-
ንብረት ታፈረ
ይርጋ ሻረው
አለምነሽ ሙሉ

ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023

# መልዕክቶችና አስተያየቶች

## ርዕሰ-አንቀጽ

## “አንደኛውን ሲሰሙት ያፈዛል፤ ሌላኛው ያደነግዛል”

«አንደኛውን ሲሰሙት ያፈዛል፤ ሌላኛው ያደነግዛል» ይላሉ ጥንታዊያኑ አባቶች የተከታዩን ከቀዳሚው መላቅ መድመቅ ለማጉላት፡፡ የነገሮችን ወይም የጉዳዮችን ስፋትና ጥልቀት ለመግለፅ የሚደረገው ጥረት፤ የሚኬድበት ርቀት ከአንደኛው የሌላኛው መለየቱን ለማመልከት፡፡

በእርግጥም ነገሮችን የምናስተውልበትና ትርጓሜ ለመስጠት የምንሞክርበት አግባብ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ከሰው ሰው ከሁኔታ ሁኔታ ይለያያል፡፡ የአባባሉን መሠረታዊነት የተለያዩ አብነቶች ጠቅሶ ማየት ማብራራት ይቻላል፡፡ ለዚህ ከዝግጅታችን ጋር ይበልጥ ቅርበት ያለውን እና በቅርቡ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተካሄደውን ውይይት ማንሳት ወደናል፡፡ በግጭት አወጋገድና አፈታት ዙሪያ የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲዎችን ድርሻ በተመለከተው የምክክር መድረክ በውይይት መነሻነት የቀረቡትን ጥናታዊ ድሁፎች ማሳያ አድርገናል፡፡

የዌስተርን ኬፕ ዩኒቨርሲቲ ም/ቻንስለር ፕሮፌሰር ቪቬን ላዋክ በጋራ የምክክር መድረኩ ላይ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ ዩኒቨርሲቲ ኢዝ ዩኒቨርሳሊቲ “University is Universality” በሚል ርዕስ ተዋቅሯል፡፡ ርዕሱንና በሥሩ የሰፈሩትን ቁም ነገሮች የዝግጅታችን ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ አድርገናል፡፡ ተጠቃሹ የጥናታዊ ጽሁፍ ርዕስ በስያሜው ጥልቅ ትርጓሜ ይዟል፡፡ «ስም ይመርሆ ለግብር» እንደሚባለው የፕሮፌሰሯ የውይይት መነሻ ርዕስ በእርግጥም ምስል ከሳች - ግብር ገላጭ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አፍሪካና አፍሪካውያን በፀናው የትግል አቋማቸው ከአስከፊው የቅኝት አገዛዝ ቀንበር ለመላቀቅና ነፃነታቸውን ለማስከበር እንዲመቻቸላቸው ለዘመናት አንገት ያስደፋቸውን የርሃብ አደጋ ተጋላጭነት ለማስወገድ የተጓዙበት ርቀት አመርቂ የሚባል አይደለም፡፡ እርግጥ ነው ለጋራ ዕድገታቸውና ዘላቂ ተጠቃሚነታቸው በጋራና በፅናት ተንቀሳቅሰው ከዘመናት ችግራቸው አልተላቀቁም፡፡ ሰፊና ለም በሆነው መሬታቸው÷ ተዝቆ በማያልቀው የተፈጥሮ ሃብታቸውና ሰብአዊ ጉልበታቸው ሊጠቀሙም ሆነ ከተርጅነት ፈጥነው ሊወጡ አልቻሉም፡፡ ከግጭትና ብጥብጥ ተለይተው የማያውቁትና በመልካም አስተዳደር እጦት የሚሰቃዩት የአህጉሪቱ ህዝቦች ነባሩን ሂደት በመቀየር ትኩረታቸውን ወደ ልማትና ዕድገት ካቀኑ ረጅም ጊዜ አልተቆጠረም፡፡

«የጨለማው አህጉር» የሚለውን የቅኝ ገዥዎች ጭምብል አውልቀው ከጣሉም ብዙ አልቆዩም፡፡ የአህጉሪቱ ሕዝባች የሀብት፣ የጉልበት፣ የእውቀትና የጋራ ጥረት ተጠቃሚነት የተስፋ ጭላንጭል እያሳየ በመጣበት፣ በአሁኑ ወቅትም ዓለማችንን እያመሰቃቀሉ ካሉት የሃይማኖት አክራሪነትና አሸባሪነት አደጋዎች ገፈት ቀማሾች መሆናቸው አልቀረም፡፡

ማንኛችንም በግልፅ እንደምንገነዘበው ከዚሁ ከሀይማኖት አክራሪነትና ሽብርተኝነት ጋር በተያያዙ ችግሮች አፍሪካውያን ቀዳሚ ተጠቂዎች ሆነዋል፡፡ ከአንደኛው የዓለም ጫፍ ወደ ሌላኛው እንደሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ በመጣው የፅንፈኝነትና ሽብርተኝነት አደጋ አያሌ አፍሪካውያን ደማቸውን አፍሰዋል፤ ሕይወታቸውንም በከንቱ ገብረዋል፡፡ ለዚህ አልሸባብ በኬንያው ጋሪሳ ዩንቨርሲቲ ያደረሰውንና ለ148 ተማሪዎች ሕልፈት ምክንያት የሆነውን እንዲሁም ቦካሃራም በሰሜን ናይጀሪያ በአንድ አዳሪ ትምህርት ቤት 300 በሚደርሱ ልጃገረዶች ላይ የፈፀመውን ዘግናኝ ድርጊት በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ይህንኑ ከአፍሪካ አልፎ የዓለም ስጋት የሆነውን የድንፈኝነትና ሽብርተኝነት አደጋ ከምንጩ ለማድረቅ በእውቀትና ክህሎት መፍለቂያነት የማይተካ ሚና ያላቸው የአህጉሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች በቅርቡ በባሕር ዳር ሸንጎ ተቀምጠዋል፡፡ ወቅታዊውን ችግር በዘላቂነት በማስወገድ ረገድ የዩኒቨርሲቲ ተቋማቱ ሚና የላቀ እንደሆነ ባስገነዘበው የጋራ ምክክር መድረክ በሀይማኖት አክራሪነትና ሽብርተኝነት ጋር በተጐዳኝ ለአፍሪካ ሰላምና መረጋጋት መንስኤ የተባሉ ጉዳዮች በጥናት ተለይተው ቀርበዋል፡፡ መፍትሄ በመሻት ረገድ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉም በውይይት ዳብረዋል፡፡

ተቋማቱ በጣና ፎረም አዘጋጅነትና በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አስተባባሪነት ባከናወኑት የጋራ የውይይት መድረክ «ዩኒቨርሲቲ ኢዝ ዩኒቨርሳሊቲ» በሚል መነሻ የቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ከዩኒቨርሲቲያችን የቅርብና የሩቅ ተልዕኮዎች ጋር በጥብቅ ተቆራኝቶ ስላገኘነው አድንኦት ልንሰጠው ፈቅደናል፡፡ ጥናታዊ ዝግጅቱ የዩኒቨርሲቲ ተቋማት ከግለኝነትና ጠባብነት ስሜቶች እንዲሁም ከዘልማድ አሰራሮች ወጥተን የጋራ እሴቶችን የምናጐለብትባቸው በእውቀትና ክህሎት እየተመራን በጋራ ጥረት የጋራ ተጠቃሚነትን የምናረጋግጥባቸው ብሎም በሳይንሳዊ የችግር አፈታት ዘዴዎች የጋራ ተጐጅነትን የምናስቀርባቸው ሁሉን አቀፍ አስተሳሰቦች የሚገበዩባቸው ማዕከላት ስለመሆናቸው ያትታል፡፡

ተቋማቱ የገሃዱ ዓለም ማያ መለያዎች የእውቀት ግብይት ሁነኛ ሥፍራዎች እንደሆኑ ይነግረናል፡፡ እኛም ዩኒቨርሲቲያችን የሩቅና የቅርብ ተልዕኮዎቹን ለማሳካት የሰው ኃይል ልማት አቅጣጫውን በዚሁ አግባብ መምራት እንዳለበት ማስገንዘብ ወደናል፡፡ ከተቋሙ በየጊዜው እየተመረቁ የሚወጡት ምሁራን ከፉክክር ምክክርን የሚያስቀድሙ ኑሮአቸውን፣ አሰራራቸውን፣ እምነትና አስተሳሰባቸውን በእውቀት ላይ የሚመሰርቱ ብሎም የመልካም ተግባርና የበጐ ምግባር አምባሳደሮቻችን እንዲሆኑ በጋራ መድረኩ መነሻ ተቋማቸው ዩኒቨርሲቲ ኢዝ ዩንቨርሳሊቲ ከሚለው ብሂል ገርፎ ተጣጥሞ እንዲጓዝ አደራችንን አፅንተናል፡፡

## ቁልፍ መልዕክት

## ሴቶች በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

ዩኒቨርሲቲያችንን በመሠረታዊነት ቀይረን ለሀገራችን ዕድገት ጠንካራ አሻራ የሚያስቀመጥ ተቋም ለመገንባት የምንከተለው መንገድ የራዕይ ጥበብ 2017 እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ለመሆኑ ይህ ራዕይ የህብረተሰቡ አንድ ትልቅ አንቀሳቃሽና መሠረት የሆኑትን የሴቶችን ሚና እንዴት ያስቀምጠዋል? በተግባርስ ምን ሠርቷል? ወዘተ. የሚሉ ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀርም፡፡ የሴቶች ሚና ጠንካራ የቴክኖሎጂ መሠረት ያለው የበለፀገ ሀገር ለመገንባት የማይተካ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ሴቶችን በሚገባ ሳያሳትፍ የተገነባና የበለፀገ የሚባል ሀገር የለም፡፡ እንዲሁ ከመሬት በተገኘ የነዳጅ ሀብት የበለፀጉ የሚመስሉ ነገር ግን የቴክኖሎጂም ሆነ አጠቃላይ የአስተሳሰብ ከፍታቸው ያላደጉትን ካልጠቀስን በስተቀር ምክንያታዊ ሀብት ያከማቹት ሁሉ ብልጽግናቸው በሴቶች ከፍተኛ ተሳትፎ የመጣ ነው፡፡ የዚህ ጽሑፍ አላማ የሴቶችን ሚና ከተለያዩ ሀገራት ዕድገት ጋር አስተሳስሮ በማቅረብ በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ በተማሪነት፣ በመምህርነት፣ በተመራማሪነት፣ በአመራርነትና በባለሙያነት የሚሰሩ ሴቶቻችን ራዕይ ጥበብ 2017 እንዲሳካ ሚናቸውን እንዲወጡ ብሎም ተሳትፏቸውና ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ የሚያደርግ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የምንከተለውን አቅጣጫ በማመላከት የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ ለስኬቱ እንዲረባረብና በሂደትም አቅጣጫውን የሚያዳብርበትን አግባብ ለመፍጠር ነው፡፡

ለዩኒቨርሲቲው መፈጠርም ሆነ ለሁላችን የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባላት የስራ ዕድል ማግኘት ምክንያትና መሠረት ከሆኑት ሴት ተማሪዎች ብንጀምር የማይተነኩሱ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ አመራሮችና ባለሙያዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ የማይተነኩሱ የታክሲና የባጃጅ አሽከርካሪዎች፣ የከተማ ነዋሪዎችና አጠቃላይ ሰላማዊና ያለምንም ስጋት የሚንቀሳቀሱበት ከባቢያዊ ሁኔታ እንዲረጋገጥላቸው የግድ ይላል፡፡ ይህ አይነት ከፆታዊ ትንኮሳና ጥቃት ስጋትና አጋጣሚ የፀዳ የዩኒቨርሲቲ ድባብ ወይም ሁኔታ ለሴት መምህሮቻችን፣ አመራሮቻችንና ባለሙያዎቻችን ሊኖር ይገባል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ውሃ ያለው መፀዳጃ ቤት፣ ልብስ ማጠቢያ ቦታ፣ የሚዝናኑበትና ስለትምህርትና ምርምር እርስ በርሳቸው የሚወያዩበት ምቹ አካባቢ ሊኖር ይገባዋል፡፡

በራዕይ ጥበብ 2017 ቅኝት ተስማሚ ከባቢያዊ ሁኔታ ለሴቶች ከመፍጠር ጐን ለጐን ቁጥራቸውን ለማበራከት ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን በመወሰን ብዙዎች ዩኒቨርሲቲውን እንዲቀላቀሉ ተደርጓል፡፡ “በአፈስሽ አይደለም በቆረጠምሽ ነው” እንደሚባለው ዋናው ጉዳይ ያሉትን ሴት መምህራንና ባለሙያዎችን ከማቆየት አንፃር ምን ይደረጋል? ሴት ተማሪዎች የሚመርጡት ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ ምን ይደረጋል? የሚሉት ጥያቄዎች መሠረታዊ ናቸው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ዩኒቨርሲቲው ለፆታዊ ትንኮሳና ጥቃት ምንም ትዕግስት የለውም፡፡ ይህን ድርጊት በሚፈጽሙ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባላት ላይ አፋጣኝና አስተማሪ እርምጃ ዩኒቨርሲቲው ይወስዳል፡፡ ሴት ተማሪዎቻችንንም ሆነ መምህሮቻችንን/ሠራተኞቻችንን መተንኮስ በራእይ ጥበብ 2017 ቀይ መስመርን ማለፍ ተደርጐ የሚወሰድ ሲሆን ይህ አቋም በተግባርም ታይቷል፡፡ ለዚህ ቁርጠኛ እርምጃ ስኬትና ዘላቂነት የሴቶች ንቁ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ ከግቢ ውጭ ያለውንም ሁኔታ ተስማሚ ለማድረግና ለመቀየር ከባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ጋር በመሆን የተቻለው ሁሉ እየተሠራ ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ሴቶችን ማስተማር ህብረተሠቡን ማስተማር ነውና ሴቶችን ማብቃት ህብረተሰቡን እንደማብቃት ይቆጠራልና ሴቶች ከወንዶች ጐን በዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማር፣ የጥናትና ምርምር፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የመልካም አስተዳደርና አመራር ጉዳዮች የሚኖራቸው ተሳትፎና ድርሻ ወደ ተሻለና የላቀ ደረጃ እንዲሸጋገር እንዲሁም የስርአተ ፆታ እኩልነትና ፍትሃዊነት እንዲሰፍን በራእይ ጥበብ 2017 ትኩረትና ቅድሚያ ተሠጥቶት የሚሠራ ይሆናል፡፡

**ራዕይ ጥበብ 2017ን**

**እናሳካለን!**

# አበይት ዜናዎች

## ጽ/ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ክበብ በደብረታቦር ከተማ መሰረተ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ከሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ ጋር በመተባበር በደብረታቦር ከተማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ክበብ መሰረተ፡፡

የምስረታ ጉባዔውን የከፈቱት የደብረታቦር ከተማ ምክትል ከንቲባ አቶ ደሳለኝ አበበ ለመምህራኑ የተሰጠውን የሙያ ማበልጸጊያ ስልጠና የሰጡትን መምህራንና ዩኒቨርሲቲውን አመስግነው በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው በአማርኛ ቋንቋ እድገት ላይ በተለይም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቋንቋ እንዲሆን እየሰራ ያለው ስራ የሚያኮራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ መምህራኑ ለቋንቋው ክብር መስጠት እንዳለባቸው በመጠቆም በቋንቋው ትምህርትና እድገት ላይ ከባሕርዳር ዩኒቨርሲቲና ከበጌምድር ኮሌጅ ጋር በመሆን የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ማድረግ እንደሚገባቸው ያሳሰቡት አቶ ደሳለኝ አስተዳደሩና ትምህርት ጽ/ቤቱም ቋንቋውን፣ የቋንቋውን ትምህርትና የመምህራኑን ሙያ ለማበልጸግ በሚደረገው ሂደት የሚጠየቀውን ሁሉ እንደሚያሟላ ቃል ገብተዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የማሕበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር ዶ/ር ጌታቸው ፍስሐ የደብረታቦር ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ባለሙያዎች፣ ምክትል ከንቲባውና የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህራን ስልጠናውን በማመቻቸትና በመከታተል ያደረጉት አስተዋጽዖ ከፍተኛ በመሆኑ ምስጋና አቅርበው እንዲህ አይነቱ አርአያነት ለሌሎች ዞኖች፣ ትምህርት ቤቶችና ከተሞች ላሉ ሃላፊዎች እንደሚሆን ገልጸዋል፡ ፡ የሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ ዲን ዶ/ር ስዩም ተሾመ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው የአማርኛ ቋንቋን ለማበልጸግ ከዚህ ፕሮጀክት በተጨማሪ በተቋም ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ማበልጸጊያ ተቋም /አቋማተ/ መስርቶ ከፍተኛ ስራ ለመስራት ማቀዱን ጠቁመው በቋንቋ በመደበኛ ትምህርት በመጀመሪያ፣ በሁለተኛና በሶስተኛ ዲግሪ እየሰጠ በመሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ገልጸዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የማኅበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር፣ የሂዩማኒቲስ ፋካሊቲ ዲን፣ የአማርኛ ቋንቋ ት/ክፍል ተጠሪ፣ የአማርኛ ቋንቋ ማበልጸጊያ ዳይሬክተርና የፕሮጀክቱ አስተባባሪ፣ የትምህርት ጽ/ቤቱ ሃላፊና ምክትል ከንቲባ፣ የበጌምድር የአስተዳደርና የስልጠና ዘርፍ ምክትል ዲንና የክበቡ ምክትል ሊቀመንበር የክበቡን ምስረታ በጋራ አብስረዋል፡፡

የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ዶ/ር ሂሩት ካሳው ለክበቡ አባላትና ወጣቶች በግልና በቡድን የሚያነቡበትና የስነ ጽሑፍ ስራዎችን የሚፈጥሩበትና የሚያቀርቡበት፤ የክበቡ መምህራን ጉልበታቸውንና አዕምሯቸውን አስተባብረው በመስራት ለከተማው ውበትም ሆነ ለማሕበረሰብ አዕምሮ ልማት አስተዋጽዖ የሚያደርጉበት እንዲሁም ጎን ለጎን ለክበቡ የገቢ ማመንጫ በመሆን የሚያገለግል በመምህራኑና በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ የሚለማ ‹የማንበቢያ አረንጓዴ መናፈሻ ቦታ›› ለክበቡ እንዲሰጥ ሃሳብ ያቀረቡ ሲሆን ምክትል ከንቲባውም አማርኛ ከመግባቢነቱ አልፎ የከተማ ልማት መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ለክበቡ የተጠየቀው መሬት የከተማ አስተዳደሩ እንደሚሰጥ ቃል ገብተዋል፡፡

በሌላ በኩል ክበቡን ከትምህርት ጽ/ቤቱ በተጨማሪ በቅርብ ሆኖ ሙያዊ እገዛ የሚያደርግለትና የሚከታተለው አካል አስፈላጊ በመሆኑ ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ከበጌምድር የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል፡፡ ኮሌጁ ለክበቡ የሚሆን ቢሮ ከነሙሉ የቢሮ መገልገያ መሳሪያ እንደሚሰጥ አስታውቋል፡፡ በክበቡ ምስረታ ላይ በሰልጣኝ መምህራን ቅኔና ግጥም ቀርበዋል፡፡

ከምስረታው ቀደም ብሎ ከጥር 7- 10/2007 ዓ.ም ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል  እንዲሁም ከግንቦት 1-5/2007 ዓ.ም ድረስ ከ5-12ኛ ክፍል አማርኛን ለሚስተምሩ መምህራን የሙያ ማበልጸጊያ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን ክበቡንም የመሰረቱት እነዚህ በሁለት ዙር ስልጠናውን የተከታተሉ መምህራን ናቸው፡፡

## ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የቴሌቪዥን ዝግጅት ሊጀምር ነው

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጅክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ከአማራ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ጋር በመተባበር በአማራ ቴሌቪዥን የሚተላለፍ “መስኮተ ጥበብ” በሚል ሥያሜ የ30 ደቂቃ የቴሌቪዥን ዝግጅት በይፋ ለመጀመር የመክፈቻ መረሃግብር አካሄደ፡፡

በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ተገኝተው የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ‘መስኮተ ጥበብ’ ከዩኒቨርሲቲው ወደ ማኅበረሰቡ ከማኅበረሰቡ ወደ ዩኒቨርሲቲው የጥበብ ልውውጥ የምናደርግበት የመገናኛ መስኮት በመሆኑ በከፍተኛ ትኩረትና ጥንቃቄ በዘላቂነት እናከናውነዋለን ብለዋል፡፡

የአማራ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ም/አስኪያጅ አቶ ደረጀ ሞገስ “መስኮተ ጥበብ” የቴሌቪዥን ፕሮግራም ዩኒቨርሲቲው ከድርጅታቸው ጋር በመተባበር መጀመሩ እንዳስደሰታቸው ተናግረው ዝግጅቱ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሀገሪቱ የመጀመሪያው ያደርገዋል ብለዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጅክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ የቴሌቪዥን ዝግጅቱን አላማ ሲያስረዱ “ዩኒቨርሲቲው በመማር ማስተማር፣ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት የሚያከናወናቸውን ሥራዎች እያዝናኑ የሚያስተምሩና የሚያሳውቁ ዝግጅቶችን በማቅረብ የዩኒቨርሲቲውን መልካም ገፅታ ይገነባል፡፡ ይህንንም ለማከናወን የዩኒቨርሲቲው እንቅስቃሴ ላይ ወቅታዊ መረጃዎችን በወቅቱ በመሰብሰብና በማጠናቀር በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ለሚገኝ ማኅበረሰብ በወቅቱ ያደርሳል፡፡ በዚህም የዩኒቨርቲዉን ራዕይ ለማሳካት ድጋፍ እና ተሳትፎ የሚያደርግ ማኅበረሰብ ይበራከታል” ብለዋል፡፡

በእለቱ ከዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ክፍሎች የመጡ መምህራን፣ ሠራተኞች፣ ተማሪዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተው የቴሌቪዥን ዝግጅቱ በመጀመሩ መደሠታቸውን ገልጸው ለቴሌቪዥን ዝግጅቱ የራሳቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሚፈልጉ ተናግረዋል፡፡

“መስኮተ ጥበብ” በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጅክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ስር በሚቋቋም የብሮድካስት ሚዲያ ዳይሬክቶሬት ከአማራ መገናኛ ብዙኃን ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው፡፡ ዳይሬክቶሬቱ የመስኮተ ጥበብ የቴሌቪዥን ዝግጅት እና በቅርቡ የሚጀመረው የማኅበረሰብ ራድዮ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፡፡ ዳይሬከቶሬቱ አቅሙን በማሳደግ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በራሱ ባለሙያዎች ቀረጻ የማካሄድና በራሱ ስቱድዮ የማቀናበር እቅድ እንዳለው ከምክትል ፕሬዘዳንቱ ጽ/ቤት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

## የፀረ ሱስ ዘመቻ ተካሄደ

በሙሉጉጃም አንዱአለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዳይሬክቶሬት ጽ/ ቤት ከዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ጋር በመተባበር «የማይጠጣበት፣ የማይቃምበትና የማይጨስበት ቀን» በሚል መሪ ቃል የፀረ ሱስ ዘመቻ አካሄደ፡፡ በዘመቻው ወቅት የእግር ጉዞና የፓናል ውይይት ተካሂዷል፡፡

በዋናው ግቢ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የፓናል ውይይቱን የከፈቱት የዩኒቨርሲቲው ኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሲ/ር ማርታ አስማረ ለተሳታፊዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት ከዲኬት ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ላሉ የደባል ሱስ ተጋላጭ ተማሪዎች ስልጠና በመስጠት ከተጠመዱበት ሱስ እንዲላቀቁ የሚያስችል ስልጠና እንደተሰጠ አስታውሰዋል፡፡ ከስልጠናው ባገኙት ግንዛቤ ከሱሱ ነፃ ሆነው ለዚህ ዘመቻ መሳካት ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳበረከቱ ገልፀዋል፡፡ ሲ/ር ማርታ አያይዘውም ጽ/ቤቱ በርካታ አመርቂ ስራዎችን እያከናወነ በመሆኑ ጉልህ ለውጦች እየታዩ ቢሆንም ከዚህ በበለጠ ጠንክሮ መስራት እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል፡፡

በውይይቱ ወቅት በደባል ሱሶች ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥኑ ጥናታዊ ፅሁፎች በመምህራን ቀርበው ሰፊ ውይይት የተካሄደባቸው ሲሆን የተለያዩ ሙዚቃዎች፣ መነባንብ፣ ግጥሞችና የተለያዩ ጽሁፎች እንዲሁም ትምርታዊ ድራማ በተማሪዎች ቀርበዋል፡፡ በዘመቻው ወቅት ተማሪዎች የተለያዩ መልዕክት የያዙ ጽሁፎችን አንግበው በዋናው ግቢ በተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር የእግር ጉዞ ማድረጋቸው ታውቋል፡፡

## ዩኒቨርሲቲው ሙያዊ ድጋፍ እንደሚያደርግ ገለጸ

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ከመንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋራ በመተባበር የአደጋ ተጋላጭነት መረጃዎችን የማሰባሰብ እና የማዘጋጀት ሥራ እያካሔደ ነው፡፡የአደጋ ተጋላጭነት መረጃዎችን የማሰባሰብና የማደራጀቱ ሥራ የከተማዋን የእለት ከእለት ለአደጋ ተጋላጭነት ቅነሳን ለማቀድና ለመቆጣጠር የሚያስችል መረጃ ለድርጅቶች እና ተቋማት ይሰጣል፡፡

አቶ ምስጋናው ተሻገር የመረጃ ማሰባሰብ እና ማደራጀት ቡድን መሪ ሥራውን አስመልከቶ እንደተናገሩት “ይህ የተቀናጀ መረጃን የመሰነድ ሥራ በድንገት ሊመጣ የሚችል አደጋን ቀድሞ ለመቆጣጠርና ለመቀነስ የሚያስችል ምቹ፣ ዘርፈ ብዙና አስተማማኝ መረጃ ያቀርባል፡፡ መረጃውም በከተማ አስተዳደሩ ደረጃ ለውሳኔ ግብአት ሆኖ ያገለግላል” ብለዋል፡፡

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዘዳንት እንደገለጹት “በቅርቡ የጸደቀውን የአደጋ መከላከል ፖሊሲ በመጠቀም የአደጋ መነሻዎችን ለይቶ በማስቀመጥና መፍትሔዎችን በመተግበር የተረጋጉና ዘላቂ እድገት ያላቸውን ከተሞች የመፍጠር ትልቅ ግብ ማሳካት ያስችላል” ብለዋል፡፡ ዶ/ር ፍቅረሰላም አያይዘውም በኢትዮጵያ ብቸኛ የሆነው የአደጋ ተጋላጭነት ቁጥጥር እና ዘላቂ ልማት ትምህርት ክፍል ያለው ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ይህ የከተማ ጥናት እንዲካሄድ አፋጣኝ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ከዚህም በላይ የዩኒቨርሲቲው የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች መከላከልና መቆጣጠር ኤጀንሲ ጋር የአቅም ግንባታና የጥናትና ምርምር ድጋፍ ለማድረግ ስምምነት ላይ መደረሱን ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የደህንነት ዋስትና የእሳት እና ድንገተኛ አደጋዎች መከላከል እና መቆጣጠር ኤጀንሲ ሥራውን ያስተባብራል፡፡ የከተማዋ ሁሉም ክፍለ ከተሞች የዚህ ስራ ተጠቃሚዎች እንደሚሆኑ ታውቋል፡፡ ለስራው የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት/ ዩ.ኤስ.ኤይድ/ የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል፡ ፡

# አበይት ዜናዎች...

## ዩኒቨርሲቲው ለፕሮፌሰር ሙሉጌታ ክብረት የእንኳን ደስ ያለዎት መርሀ ግብር አዘጋጀ

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲው ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙዩኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ፕሮፌሰር ሙሉጌታ ክብረት በአካዳሚ፣ በምርምርና ለማህበረሰቡ ባበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በዩኒቨርሲቲው ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የእንኳን ደስ ያለዎት መርሀ ግብር አዘጋጀ፡፡

የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙዩኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ በሳይንስ ኮሌጅ የስነ ሕይወት (ባይሎጂ) ት/ክፍል መምህርና ተመራማሪ የሆኑትን የፕሮፌሰር ሙሉጌታ ክብረት የህይወት ታሪክ ያቀረቡ ሲሆን እንደዚህ አይነት ስኬታማ ተሞክሮዎችን እውቅና መስጠት ሌሎች ተመራማሪዎችን ለማበረታታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸዋል፡፡ ጽ/ቤቱ በቀጣይም ለፕሮፌሰር ማዕረግ ለሚበቁ ተመራማሪዎች ይህን አይነት መርሀ ግብር እንደሚያዘጋጅ ተጠቁሟል፡፡

የሳይንስ ኮሌጅ ዲን ዶ/ር እሰይ ከበደ እንደተናገሩት ፕሮፌሰር ሙሉጌታ በኮሌጁ ቀዳሚ መምህር፣ አማካሪና ተመራማሪ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ፈር ቀዳጅና ታዋቂ ተመራማሪ ናቸው፡፡ ፕሮፌሰሩ በ2005 እና 2006 ዓ.ም ምርጥ ተመራማሪ ተብለው መመረጣቸውን አስታውሰዋል፡፡

በመርሃ ግብሩ ላይ ፕሮፌሰር ሙሉጌታ የፕሮፌሰር ማዕረግ ያደረሳቸውን የረጅም አመት ልምዳቸውንና የህይወት ተሞክሯቸውን ለተሳታፊዎች አካፍለዋል፡፡ 'The problems of Antimicrobial Resistance' በሚል ርዕስ ትምህርታዊ መግለጫ የሰጡ ሲሆን የምርምራቸውን ውጤትና የውጤቱን አስፈላጊነት በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው መምህራን በመተባበር፣ ግልጽ በመሆንና በስነ ምግባር በመታነጽ በመማር ማስተማሩና በምርምሩ ቀዳሚ እንዲሆኑ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ በእለቱ ተሳታፊዎች ለፕሮፌሰሩ የእንኳን ደስ ያለዎት መልዕክት አስተላልፈው በምርምር፣ በማማከርና በማስተማር የህይወት ተሞክሯቸውን አስመልክቶ ጥያቄዎች ቀርቦላቸዋል፡፡ ፕሮፌሰር ሙሉጌታም ምላሽ ሰጥተውበታል፡፡

የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚደንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው መርሃ ግብሩ ያዘጋጁትን የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙዩኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤትንና የሳይንስ ኮሌጅን ያመሰገኑ ሲሆን ፕሮፌሰሩ በመማር ማስተማሩና በምርምር ያላቸውን ተሞክሮ አጠናክረው በሙያቸው የማህበረሰቡን ህይወት ለማሻሻል እንደሚጥሩ ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል፡፡ ዶ/ር ተስፋዬ አያይዘውም ዩኒቨርሲቲው ለወደፊቱ በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ስኬታማ በመሆን ለፕሮፌሰር ማዕረግ ለሚበቁ ምሁራን እውቅና እንደሚሰጥ ተናግረዋል፡፡

በእለቱ የፕሮፌሰሩ ቤተሰቦች፣ የአሁንና የቀድሞ ተማሪዎች፣ የስራ ባልደረቦች፣ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በመርሃ ግብሩ ላይ ተገኝተዋል፡፡

## ዩኒቨርሲቲው መጽሐፍትን በእርዳታ አገኘ

በአበባ ሐብቱ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ World Lending Library (WLL) ከተባለ ዓለም አቀፍ ፕሮጀክት ኤሌክትሮኒክስ መጽሀፍት (e-books) (250,000 በድምፅ እና 8,000 በምስል የተቀነባበሩ የመማሪያና የምርምር መጽሐፍትን በእርዳታ አግኝቷል፡፡

ፕሮጀክቱ ለአለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ያሰባሰባቸውን መጠናቸው 2.7 TB የሚደርሱ መጽሐፍት በዋናው ግቢ የመሰብሰቢያ አዳራሽ መምህራንና ተማሪዎች በተገኙበት የፕሮጀክቱ ሀላፊ ሚስተር ጆሴፍና ባለቤታቸው ሚስዝ ናንሲ ለዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ አስረክበዋል፡፡

ዶ/ር ማተቤ ከስጦታዎች ሁሉ ስለከበረው የመጽሐፍት ስጦታ ለፕሮጀክቱ አስተባባሪዎች ምስጋናቸውን አቅርበው በዩኒቨርሲቲው ስም የተዘጋጀውን ስጦታ አበርክተዋል፡፡ በመጨረሻም ፕሮግራሙን ያስተባበሩት የዩኒቨርሲቲው አይ.ሲ.ቲ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ አጥናፉ ዓለሙ ስለተደረገው እርዳታ ድርጅቱን በማመስገን በቅርብ ጊዜ መጽሐፍቱን በዩኒቨርሲቲው ሰርቨሮች በመጫን ለተጠቃሚ እንደሚያደርሱ ቃል በመግባት የዕለቱ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

## ለሴት ሰራተኞች የአመራር ስልጠና ተሰጠ

በሙሉጐጃም አንዱአለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስርዓተ ፆታ ዳይሬክቶሬት ጽ/ቤት ከዩኒቨርሲቲው ጋር በመተባበር የአስተዳደር ሴት ሰራተኞችን የአመራር ብቃት ለማጐልበት ለሁለት ተከታታይ ቀናት የቆየ በዩኒቨርሲቲው ሴኔት መሰብሰቢያ አዳራሽ ስልጠና ሰጠ፡፡

የስልጠናውን መክፈቻ ንግግር ያደረጉት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ምህረቴ ዋለ ተሳታፊዎች፣ አሰልጣኞችና ሰልጣኞች የጽ/ቤቱን ጥሪ አክብረው በመምጣታቸው የምስጋና መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን የሴቶችን የአመራርነት ብቃት ለማጐልበት ዩኒቨርሲቲው በቁርጠኝነት እየሰራ በመሆኑ ስልጠናው የዚህ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡ አቶ ምህረቴ አክለውም ሴቶችን ወደ አመራርነት ለማምጣት ክህሎታቸውን ማሳደግ ቀዳሚ ተግባር ስለሆነ ስልጠናው የመሪነት ችሎታቸውን ከማበልፀግ ባሻገር ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባሕላዊና ማሕበራዊ ችግራቸውን ለመፍታት ጉልህ አስተዋፅኦ እንዲኖረው ታልሞ መዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

አሰልጣኞቹ በበኩላቸው የዩኒቨርሲቲው እቅድ የሴቶችን የአመራርነት ተሳትፎ ሰላሳ በመቶ ማድረስ ቢሆንም በተጨባጭ ያለው ውስን በመሆኑ ሰልጣኞች ከስልጠናው የአመራር ፅንሰ ሀሳብ፣ የስኬታማ መሪ መርሆዎች፣ የአመራር ዘይቤዎችና ሴቶች ወደ አመራር እንዳይመጡ የሚያግዱ እንቅፋቶች ምን እንደሆኑ ግንዛቤ እንደሚያገኙ ተናግረዋል፡፡

በስልጠናው ወቅት የስርዓተ ፆታን ምልከታ መሰረት በማድረግ በርካታ ሀሳቦች የተነሱ ሲሆን ተሳታፊዎች እንደገለፁት ከስልጠናው ሴቶች ደረጃ በደረጃ ወደ አመራርነት እንዳይሸጋገሩ የሚያደርጉ መሰናክሎች ምን እንደሆኑና በለውጡ ሂደት ላይ መሪዎች ያላቸው ሚና ያለበትን ደረጃ ማወቅ እንደቻሉ እንዲሁም ሴቶች ያላቸውን አቅም ከተጠቀሙበት መምራት እንደሚችሉ መገንዘባቸውን ተናግረዋል፡፡

## የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ አገር አቀፍ ጉባዔ አካሄደ

በሙሉጎጃም አንዱአለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የመጀመሪያ የሆነውን አገር አቀፍ ዓመታዊ ጉባዔ "Logistics and supply chain management for Development: Achievement, challenges and prospects in Ethiopia" በሚል መሪ ቃል በዩኒቨርሲቲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ አካሄደ፡፡

የእንኳን ደህና መጣችሁና ለጉባዔው አዘጋጅ አካላት የምስጋና መልዕክታቸውን ያስተላለፉት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ የጉበዔው ዋና ዓላማ አገራችን ኢትዮጵያ በሎጅስቲክ ዙሪያ ምን ደረጃ ላይ እንዳለች የሚያሳየንና በዘርፉ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማጐልበት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ በተጨባጭ የምንለካባቸው መንገዶች እድገት፣ አስተዳደር፣ የአቅርቦት ሰንሰለትና ሎጅስቲክ ናቸው፡፡ የዕድገት መመዘኛ ነጥቦች ደግሞ የነፍስ ወከፍ ገቢ ማደግ፣ የተሟላ የጤና አገልግሎት ማግኘትና ጥሩ ትምህርት ለሁሉም ትውልድ ማዳረስ የሚሉት ሲሆኑ አስተዳደርም ሕዝብን አቀናጅቶ በመስራት የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ዶ/ር ባይሌ አሳስበዋል፡፡

በኢትዮጵያ የኩኔ (Kuehne) ፋውንዴሽን አማካሪ አቶ ባህረ ገሰሰ ሎጅስቲክ በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል የገለጹ ሲሆን ዋናው ማሰሪያ መሰረተ ልማትና የመሰረተ ልማቱ ውጤት ስለሆነ በአገራችን ያለው አሰራር በዘመናዊ መንገድ ሳይሆን በዘልማድ እየተካሄደ በመሆኑ መንግስትም ሆነ የግል ተቋማት ለለውጡ ዋነኛ መፍትሄ የሆነው ሙያዊ ብቃት እንዲኖር ለማድረግና የአሰራር ቅንጅት በመፍጠር ለሀገሪቱ ትልቅ ፀጋ የሆነውን ወጣቱን ትውልድ ለማብቃት ርብርብ እንደሚያስፈልግ አስረግጠው ገልፀዋል፡፡ አቶ ባህረ አክለው ከኢኮኖሚው እድገት ቀድሞ መምጣት ያለበት የሎጅስቲኩ መጠናከር ነው፡፡ በተጨባጭ ያለው ሁኔታ ግን የሎጅስቲኩ የተዳከመ መሆን ችግሩን ለመፍታት መንግስት የድርሻውን በመውሰድ እንዲሁም በእርሻም ሆነ በኢንዱስትሪ የተሰማሩ አካላት ከየአቅጣጫው ትኩረት ሰጥተው መስራት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

በጉባዔው ላይ የአቅርቦት ሰንሰለቱንና የሎጅስቲክ ቀመሩን ለማስተካከል ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ የተለያዩ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡ አንዳንድ የኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች እንደገለፁት አገሪቱ የምትከተለው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ግብ እንዲመታ እንዲሁም በሎጅስቲክ በኩል የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ጉባዔው ጉልህ ሚና እንዳለው የገለጹ ሲሆን የቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፎችን ወደ ተግባር መለወጥ ተገቢ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

# ህይወት (አጭር ልቦለድ)

በሰሎሞን ንጉስ (ዋኒ)

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ት/ክፍል እጩ ምሩቅ

ስልኬ … አቃጨለ…! የስልኬ መጥሪያ ያደረኩት የምወደው የቴዎድሮስ ካሳሁን ዘፈን ስለነበር ሙዚቃውን ለመስማት ዘግይቼ ነበር ስልኩን ያነሳሁት::

“ጤና ይስጥልኝ …» የሴት ድምፅ ነበር::

“አብሮ ይስጥልኝ …! ማን ልበል …?”

“አታውቀኝም::”

“እና ለምን ደወልሽ…?”

“ላደንቅህ”

ግራ ተጋባሁ ብዙ ጊዜ ካምፓስ ውስጥ ችኮች ሙድ ለመያዝ ይደውሉና ‘አታውቀኝም እኔ ግን አውቅሃለሁ::’ እያሉ ስለሚቀበጣጥሩ ያው የእነሱ ብጤ ትሆናለች ብዬ ስልክን ልጠራቅመው ስል …!

“ስማኝ ከምሬ ነው አታውቀኝም”

“እና አንቺ እንዴት አወቅሽኝ አልኳት በቁጣ…?”

ድምጿን ለዘብ አድርጋ የሰራኸውን ፊልም አይቼ ነው:: “ትንሽ አስተያየት እና አድናቆት ልቸርህ ፈልጌ ነው ከፈቀድክልኝ …?” ማውራቷን ቀጠለች:: እና ምን መሰለህ ስራው እንደ ጀማሪ አሪፍ ነው ድምፅህ ለፊልም የተዋጣለት ነው በተለይ ከፊልሙ በፊት የሰራኸው ማስታወቂያ እንዴት ደስ እንደሚል ልነግርህ አልችልም:: ጥሩ አስተዋዋቂ ትሆናለህ ትወናህም በጣም ደስ ይላል በተለይ የእብዱን ካራክተር በጣም ተዋጥተኸዋል:: በቃ ምን ልበልህ ፍቄሜህን ያሳምረው:: ለወደፊቱ የበለጠ ነገር እጠብቃለሁ:: ልታሻሽላቸው የሚገቡ ነገሮች ደግሞ ሌላ ጊዜ ደውዬ እነግርሃለሁ:: ለዛሬ አድናቆቴ ይህንን ይመስላል:: አመሰግናለሁ::”

በደንብ ነው የሰማኋት “ግን አሁንም አልተዋወቅንም” አልኳት “እ…እ.. ህይወት እባላለሁ:: በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የ2ኛ ዓመት የአርት ተማሪ ነኝ:: እና ፊልምህን ያየሁት አንተ ጋር የተወነችው ጓደኛዬ ስለነበረች እና አንድ ቲያትር ቤት ስለምንሰራ እሷናት ያሳየችኝ:: ከዚያ ስልክህን ተቀብያት ደወልኩልህ:: ብቻ ስለ አንዳንድ ነገር እየተደዋወልን እናወራለን…! ብላ ስልኩን ጠረቀመችው::

ህይወት …! ህይወት …! ጥሩ ሴት እንደተዋወኩ ተሰማኝ:: የረሳሁትን እንደሙከራ የሰራነውን ፊልም አይታ አስተያየት ስለሰጠችኝ አመሰገንኳት::

ወራቱ ክረምት ስለነበር ለእረፍት ክፍለ ሀገር ነው ያለሁት:: እረፍት ተባለ እንጂ አሁንም ከትምህርት የከፋ ሥራ አጋጥሞኛል:: ቁጭ ብዬ አባዬን መጠበቅ:: አባቴ በከተማ የሚታወቅ ስመ ጥር ነው:: ስመ ጥሩነቱም በርካታ ልጆች በመወለዱ ነው:: ከእናቴ ስድስት፣ ከእከሊት አራት፣ ከሌላኛዋ አምስት እንዲሁም …ብቻ! በድምሩ ሃያ አንድ ልጆች አሉት:: ሌላው ቢቀር ኤርትራም ሁለት ልጆች አሉት:: ይህ ስመጥር ዛሬ የአልጋ ቁራኛ ሆኗል• ክፉኛ ታሟል:: ልጆቹ ቤተ ዘመዶቹ ሁሉም እሱን እያስታመምን ነው:: እኔም ለአዘቦት ወደ ክ/ሀገር ሄድኩ እንጅ አንዴም አላረፍኩም:: ከአባቴ ጐን ቁጭ ብዬ ሃያ አራት ሰዓት እንቅልፍ በዓይኔ ሳይዞር አስታምመዋለሁ::

> ምን እንደነካኝ ባላውቅም የህይወት ድምፅ ካልሰማሁ ቀኑ ቀን ሌቱ ሌት አልመስል ይለኝ ጀመር:: የምነግራት ነገር ቢጠፋኝ እንኳ ደውዬ ግጥም አነብላታለሁ:: የህይወት ምስል በህሊናዬ / በምናቤ/ ሳልኩት ጠይም መልከ መልካም ፅጌረዳ አበባ የመሰለች … በቃ! ራሴ የሳልኩት ምስሏ በምናቤ ድቅን ይልብኛል …

ብቻ ከአባቴ ጐን አልጠፋም፣ ውሃ ካለኝ ውሃ አቀርባለሁ፣ ሌላም ሌላም ያሻውን አቀርብለታለሁ:: ወደ ሌሊት ስድስት ሰዓት አካባቢ ጣረ ሞት ያዘው:: ሁላችንም እንደማይተርፍ ስላሰብን ለቀብር ሥነ-ሥርዓቱ አስፈላጊውን ቁሳቁስ ማሰናዳት ጀመርን:: አባቴ ከተናዘዛቸው ኑዛዜ የመጨረሻው የህልፈተ ህይወቱ ድምፅ እንዲህ የሚል ነበር::

…ኸ…ህ …! ልጄ “በረከት” አንተ የመጨረሻ ልጄነህ እናም ይህንን ዳዊት፣ መፅሐፍ ቅዱስ ያዝ! ድገመው ህይወት ይሆናሃል በምትጓዝበት መንገድም ይመራሃል::» እምባ በዓይኖቼ ይፈስ ጀመር:: በጣም ጨነቀኝ ሰው እንዲህ ሞት አፋፍ ላይ ደርሶ ሲናዘዝ ሳይ የመጀመሪያዬ ነበር:: #ልጆቼ …! ደብቄያችሁ የኖርኩት አንድ ምስጢር አለ:: ወታደር እያለሁ የወለድኳት ልጅ አለችኝ:: ብዙ ወንድሞች እና እህቶች አሉሽ:: አንዴ አስተዋውቅሻለሁ እያልኳት ሳላስተዋውቃችሁ ድንገት ቀኝ እጄ ከዳኝ:: እስከ ዛሬ ድረስ ደብቂያችሁ ነበር:: ዳሩ አልጠቀመኝም:: ከወር አንድ ጊዜ እህቴን ልጠይቅ እያልኩ የምሄደው ልጄን ለማግኘት ነበር:: እናም ልጆቼ ልጄ! እናንተ መተዋወቅ ትሻለች በረከት ልጄ አንተ ለኔ ታዛዥ ነህ እንደምንም እህትህን ፈልገህ አግኛት:: የእኔን አድራሻ በጭራሽ አታውቀውም:: የሷ አድራሻና ስሟ ግን… » ብሎ እጅን ወደፈለገው አቅጣጫ ሳይቀስር በዚያው አሸለበ:: ቤቱን በኡ…ኡ…ታ አቀለጥነው ከአባቴ ሞት በላይ የእግር እሳት የሆነብኝ የእህታችን ስምና አድራሻ ሳይነግረን ማሸለቡ ነው:: ቤት ውስጥ አባቴ ያስቀመጣቸው መፅሐፍት፣ ሳጥን ውስጥ የቀረኝ ወረቀት የለም የእህታችን አድራሻ ሳላገኘው ቀረሁ:: ከሳምንታት በኋላ ዩኒቨርሲቲዎችን ስለጠራን ታላቅ ወንድሜ እንደ ምንም ብሎ አድራሻውን አፈላልጐ እንዲነግረኝ ቃል አስገብቼው ወደ ግቢ ሂድኩ:: መንገዱ አድካሚ እና አሰልቺ ስለነበር ሻወር ምናምን ወሳጄ አረፍ እንዳልኩ ስልኬ ጮኸ…!

ሃሎ …! ማን ልበል?

ማን ልበል?

አዎን …! አላወኩሽም !

“Thank you …!»

“ለምኑ…?»

“ስለረሳኸኝ ለማንኛውም ህይወት ነኝ::»

“ኦ…! ሂዊዬ … ይቅርታ!

ሰላም ነው …? ስልክሽን ሴቭ (Save) ስላላደረኩት ነው::» “አይ … no problem::» ስልኩ ተቋረጠ:: ህይወት በጣም ጥሩ እንስት ነች! እኔ ሳልደውልላት እሷ አልፎ አልፎ ቢሆንም ትደውልልኛለች:: ከህይወት የወደድኩላት ነገር ቢኖር የጥበብ ሰው መሆኗን ከዚያ ደግሞ ጥሩ አንባቢ እና ገጣሚ መሆኗ ነው:: አንዳንዴ አስተያየት ስጠኝ እያለች የምታነበንብልኝ ግጥም ዘወትር ከህሊናዬ አይጠፋም:: በተለይ ደግሞ ከእኔ ጋር ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አብራኝ የምትማረው ጓደኛዋ ሰናይት ስለሷ መልካምነት ስትነግረኝ ይበልጥ ልቡናዬ ላይ ትቀረፃለች:: ምን እንደነካኝ ባላውቅም የህይወት ድምፅ ካልሰማሁ ቀኑ ቀን ሌሊቱ ሌሊት አልመስል ይለኝ ጀመር:: የምነግራት ነገር ቢጠፋኝ እንኳ ደውዬ ግጥም አነብላታለሁ:: የህይወት ምስል በህሊናዬ /በምናቤ/ ሳልኩት ጠይም መልከ መልካም ፅጌረዳ አበባ የመሰለች … በቃ! ራሴ የሳልኩት ምስሏ በምናቤ ድቅን ይልብኛል:: ወይ ድፍረት በድምጿ ብቻ ወደድኳት፤ ወይ አጋጣሚ ፍቅርም እንዲህ ሆነ…? ነገሩ ፍቅር መቼ ታስቦበትና ታልምበት የሚከወን ድርጊት ሆነ::

ደስ የሚል ሰርፕራይዝ ደውዬ አበሰርኳት:: አዳማ ላይ ለሚካሄደው ስድስተኛው ሀገር አቀፍ የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ስፖርት ፌስቲቫል የአካባቢውን ቋንቋና ባህል ለማሳየት በግቢያችን ባለው የባህል ማዕከል በተዋናይነት ተመርጭ አዳማ እንደምሄድ ነገርኳት:: እሷም እንደተደሰተች ነገረችኝ የማላውቃትን አዲስ አበባን ሳይሆን በድምፅ ብቻ የማውቃትን ህይወት ለማየት ጓጓሁ:: ምሽት 12:30 አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ገባን:: ወዲያውኑ ደወልኩላት … ቅፅበት ሳይቆይ ከሰማይ እንደወረዳ መና “በረከት” አለችኝ! የማላውቀው ስሜት መላው አካላቴን ወረረኝ … አቤት … ተፈጥሮ! አቤት … ወዘና! አቤት ቁንጅና! አቤት … ቁመና! ሰላምታ ተለዋውጠን እና ሻንጣዬን አስቀምጬ እራት ለመብላት ወደ ከተማ ወጣን:: “በረከት» አለችኝ:: በፈገግታ መለስኩላት:: “ለምን ካልደከመህ ቲያትር አናይም?» ስትለኝ ግብዣዋን ተቀብዬ ብሔራዊ ቲያትር “ባቢሎን በሳሎን” የሚለው ታዋቂ አርቲስቶች የተሳተፉበት አዝናኝ ቲያትር አይተን እራት ለመብላት ወደ ሆቴል አመራን:: እራት እየበላን ማወራረጃ አንድ ሁለት ጃንቦ ጠጣን:: የልብ የልባችንን ስናወራ ሰዓቱ ከንፎ ከምሽቱ 6:30 ሆኗል:: ሰዓት እንዳየች ደነገጠች:: የግቢው በር በመዘጋቱ መደንገጧ ቅፅበታዊ ቢሆንም እኔ ከጐኗ ስላለሁ የደስ ደስ ይነበብባታል:: አይዞሽ አትስጊ አልጋ ይዘን አብረን እናድራለን ብዬ አግባብቼ ወደ መኝታ ክፍል ይዣት ሄድኩ:: ስለደከመኝ አልጋው ላይ ተዘረርኩ ህይወት አንገቷን አቀርቅራ ትተክዛለች … “ችግር አለ? … ህይወት» አልኳት ምላሽ አልሰጠችኝም እጆቿን ጨበጥ አድርጌ ወደ አንገቴ ስር ለጠፍኳት ትንፋሿ ይበልጥ ስሜቴን ለኮሰው:: እኔም አንገቷ ውስጥ ተለጥፌ፣ ትንፋሽ ለትንፋሽ ተለዋዋጥን፣ ተሳሳምን፣ ተጋጋልን አሰቡት ! ሁለት ተቃራኒ ፆታዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ተኝተው ምን እንደሚፈጠር…? ቀስ በቀስ ሙዳችን እየተቀየረ ስሜታችን እየጋለ መጣ…! በቃ ያለምንም ጥያቄና መልስ የሥጋ አምኖታችንን ተወጣን:: ህይወት የመጀመሪያዬ ነበረች:: እሷም ከኔ ውጭ ወንድ እንደማታውቅ አንሶላው ላይ የተነከረው ፈሳሽ ማረጋገጫ ነው:: የወደቅንበት እንኳን ሳናውቅ ሌሊቱ ተጠናቀቀ:: ጠዋት ስልኬ ሲጮህ ነበር የነቃሁት ታላቅ ወንድሜ ነበር:: ስልኩን አንስቼ ባናግረው አልተሰማኝም:: ድጋሚ ደወለ አሁንም እንደዛው … ኔትወርክ ሲያስቸግረው እንዲህ ሲል ቴክስት ፃፈልኝ:: እንኳን ደስ አለህ ወንድሜ! የእህታችን አድራሻ እና ስልክ ቁጥር ከአባቴ መፅሐፍ ውስጥ አገኘሁት ብሎ አድራሻዋን እና ስ.ቁ ላከልኝ … ስልክ ቁጥሩን እንዳየሁት ማመን አቃተኝ …! አብራኝ አንሶላ የተጋፈፈችው የህይወት ስልክ ነው::

ለካ አንዳንዴም … ህይወት እንዲህ ናት ህይወት አጋጣሚ-አጋጣሚ ህይወት::

# ፈለገ ህይወት ሆስፒታል - አይሞላልሽ ባተሌ?

ጀማል ሙሀመድ ሀይሌ (ዶ/ር)
ከጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል
jemalmohammed99@gmail.com

ከአስራ አምስት አመት በፊት ነው። የህዝብ ማመላለሻ አውቶቡሱ በወረታ-ወልድያ የጠጠር መንገድ ላይ የቻለውን ያህል እየሮጠ ነው፤ በጎርበጥባጣው መንገድ ላይ በሮጠ ቁጥር ተሳፋሪዎቹን ሳይወዱ በግድ እያስደለቃቸው፣ እንደሚገፋ እርጎ ወዲያና ወዲህ እየናጣቸው ነው፤ በአራት እግሮቹ እያግተለተለ ከሚያቦለው አቧራ ውስጥ የተወሰነውን ወደ ውስጡ እያስገባ እያጠናቸው ነው። እዚያ ካለነው ተሳፋሪዎች መካከል ከመንገዱ "አለመሰልጠን" እና ከመኪናው አሮጌነት የመነጨውን የጉዞ ስቃይ ብዙም ልብ ያላሉት የሚመስሉት ከፊቴ ካለው ወንበር ላይ የተቀመጡ አንድ በእድሜ የገፉ ሰውዬና ከጎናቸው ያለ ወጣት ናቸው። የሞቀ ወሬ ይዘዋል። በወሬ፣ ወሬ ስለቃላትና ስለሚሸከሙት መልእክት መጨዋወት ጀመሩ። ሰዎቹ ሳይታሰብ፣ በወሬያቸው መሀል ወደ ሙያዬ ጠጋ-ጠጋ ማለት ስለጀመሩ፣ ጆሮዬን ጣል አድርጌ ማዳመጥ ጀመርኩ።

ሰውዬው "ቢዚ" (busy) የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል በአማርኛ እንዲተረጉምላቸው ጠየቁት - ወጣቱን። እሱም "በስራ የተጠመደ"፣ "ስራ የበዛበት"፣ "ፋታ በሌለው ስራ የተያዘ"... በማለት ለመተርጎም ሞከረ። ሰውዬው "በአንድ የአማርኛ ቃል ብቻ ተርጉምልኝ" አሉት። አሰበ፣ አሰበ፤ ሊያገኝ ግን አልቻለም። የወጣቱን መረታት ለማስረገጥ በሚመስል ሁኔታ፣ ለተወሰነ ጊዜ ፀጥ አሉ።

ከዚያም "'ቢዚ'ን አሳምሮ የሚተረጉም የኛ የወሎዬዎች ቃል አለ" አሉት።

"ምን የሚል?"

"ባተሌ!"

ወጣቱም ቃሉን ደጋገመው፣ "ባተሌ፣ ባተሌ..."

እናም ሰውዬው፣ በወጣቱ ላይ ትንሽ ተኩራሩበት፤ "ይሄውልህ እኛ ወሎዬዎች ባማርኛ እንዲህ ሀብታም ነን።"

በሚያዚያ ወር 1955 በቀዳማዊ ሀይለስላሴ ተመርቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረውና በአማራ ክልል ርእሰ ከተማ - ባህር ዳር - የሚገኘው የፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል ባተሌ ነው፤ ሌሊት የለ፣ ቀን የለ፤ ሲታትር ውሎ፣ ሲታተር ያድራል። ላለፉት 52 አመታት እጣ ፈንታው ይህ ነበር፤ አሁንም ነው፤ ነገም ይቀጥላል።

ያኔ የተሰራው ለ25 ሺህ ህዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ ሲሆን፣ አሁን ግን እስከ ሰባት ሚሊየን ለሚደርስ ህዝብ አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ መረጃዎች ያመለክታሉ። ተኝቶ ታካሚዎችን ጨምሮ፣ በአሁኑ ሰአት በየቀኑ በአማካይ ለአንድ ሺህ ህሙማን የህክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። እናም ሆስፒታሉ በጣም ባተሌ ነው፣ የባተሌም ባተሌ። ባተሌነቱ ፍሬ እንዲያስገኝ የሚያደርጉ ሁኔታዎች እንዳሉ ሁሉ፣ "ውሀ ቢወቅጡት እንቦጭ" የሚያደርጉ ችግሮችም አሉበት - አምናና ዘንድሮ በሆስፒታሉ በነበረኝ የአስታማሚነት ቆይታዬ የተረዳሁት ይሄን ነው። ትዝብቴን ላጫውታችሁ መነሳቴም ለዚሁ ነው...

የፈለገ ህይወት የተኝቶ መታከሚያ ክፍሎች ቆይታዬ የተረዳሁት እውነታ የሚመሰክረው ይህ የቀድሞ "ታሪክ" እየተቀየረ መሆኑን ነው። በአስትማሚነት ቀይታዬ እንደታዘብኩት፣ በተኝቶ መታከሚያ ክፍሎች ውስጥ ዋናውን ተግባር ተሸክመው ያሉት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህክምና ሳይንስ ተማሪዎች ናቸው።

## የፅዳት ሰራተኞች

ሆስፒታሎች ህሙማን ለህመማቸው ፈውስን ፍለጋ የሚሄዱባቸውና እንዳስፈላጊነቱም ተኝተው ጭምር የሚታከሙባቸው ቦታዎች ናቸው። የየትኛውም ቦታ ፅዱና ንፁህ መሆን ጤንነትን ለመጠበቅ ጥሩ ከመሆን አልፎ፣ ለመንፈስ እርካት መስጠቱ ግልፅ ነው። የዚህ አይነቱ አካባቢ ህሙማን የሚውሉበትና የሚያድሩበት የህክምና ተቋም ሲሆን ደግሞ፣ አስፈላጊነቱ በእጅጉ ይጨምራል። ንፅህናው ያልተጠበቀ የህክምና መስጫ ቦታ ወይም ተቋም በበሽታ ላይ በሽታ ሊጨምር ይችላልና ጉዳቱ ከፍተኛ ነው።

ከዚህ አንፃር የፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል የፅዳት ሰራተኞች እየተጫወቱ ያለው ሚና እጅግ የሚደነቅ ነው። የሆስፒታሉ የህሙማን መኝታ ክፍሎች፣ መተላለፊያዎች፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ በህሙማን መኝታ ክፍሎች መካከል ያሉ የአትክልት ቦታዎች... በየቀኑ ይጠረጋሉ። በተለይ የህሙማን መኝታ ክፍሎችና ክፍሎቹ ያሉበት ህንፃ መተላለፊያዎች በቀን ውስጥ በተደጋጋሚ ይወለወላሉ፤ የመወልወል ድግግሞሹን የሚወስነው "በቀን ይህን ያህል ጊዜ" የሚለው ቁጥር ሳይሆን፣ የመቆሸሹ መጠን ነው። የቆሸሸን ክፍል ወይም ቦታ የሚታገሰው የለም። ይህም በመሆኑ በፊት ወደ ሆስፒታሉ ስንሄድ ያጋጥመን የነበረው አፍንጫን የሚጠልዝ መጥፎ ሽታ የለም፤ ገና ወደ ህሙማን መኝታ ክፍሎች መተላለፊ ገባ ስንል ያጥነገንገን የነበረውን መጥፎ ጠረን ድራሹን አጥፍተውታል። እንደ እኔ ከሆነ፣ ለነዚህ የሆስፒታሉ የፅዳት ሰራተኞች ምስጋናም-ሽልማትም ሲያንሳቸው ነው።

የፅዳት ሰራተኞቹ ሙያቸውን የሚወጡት በ"የትም ፍጪው፣ ዱቄቱን አምጪው" 'መርህ' አለመሆኑ ሌላው ቁም ነገር ነው። ማለትም መስራት ስላለባቸው ብቻ፣ ደመወዝ የሚያገኙበት ተግባር ስለሆነ ብቻ አይደለም የሚሰሩት። ያላቸው ሙያዊ ስነምግባር የሚደነቅ ነው። ለዚህ ምስክርነቴ አስረጅ ላቅርብ። በአጋጣሚ አንድ የህሙማን ክፍል ወይም በክፍሉ ውስጥ ካሉት ህሙማን የአንዱ አልጋ ወይም ወለሉ ሲቆሸሽ (ደም፣ ሽንት፣ ወዘተ ሲፈስበት) በማንኛውም ሰአት መጥተው እንዲያፀዱ ሲጠየቁ፣ ፊታቸውን እንኳን ትንሽ ጠቆር አያደርጉም። አገልግሎቱንም ወዲያው ይሰጣሉ፤ የአገልግሎቱን ጥራትም አያጓድሉም።

የነዚህን አይነት የአገልጋይነት ስሜት ያለው የመንግስት ሰራተኛ መፍጠር ቢቻል በርካታዎቹ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ሀገሪቱን "ቻው" ብለው በተሰናበቱ ነበር።

## የህክምና ባለሙያዎች

በፈለገ ህይወትም ሆነ በሌሎቹ የአገሪቱ ክፍሎች ባሉ የመንግስት የህክምና ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ጥቂት የማይባሉ የህክምና ባለሙያዎች በስነምግባር ጉድለት (በወቅቱ ስራ ላይ ባለመገኘት፣ ህሙማንንና አስታማሚዎችን በማጉላላት፣ በመሳደብ ወይም በማመናጨቅ፣ ለግል ስራ አላግባብ ቅድሚያ በመስጠት፣ ወዘተ) እንደሚታሙ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ባለፈው አመትም ሆነ በዘንድሮው የፈለገ ህይወት የተኝቶ መታከሚያ ክፍሎች ቆይታዬ የተረዳሁት እውነታ የሚመሰክረው ይህ የቀድሞ "ታሪክ" እየተቀየረ መሆኑን ነው። በአስትማሚነት ቀይታዬ እንደታዘብኩት፣ በተኝቶ መታከሚያ ክፍሎች ውስጥ ዋናውን ተግባር ተሸክመው ያሉት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህክምና ሳይንስ ተማሪዎች ናቸው። በስራ ስምሪት ወረፋቸው መሰረት ተፍ-ተፍ ሲሉ ይውላሉ፣ ያድራሉ።

አገልግሎት የሚሰጡት፣ እንቅልፍ ሰውን በአፍ-ጢሙ ለመድፋት ጉልበት በሚያገኝበት በደረቁ ሌሊት፣ ከእንቅልፋቸው ተቀስቅሰው እንኳን ቢሆን የድካም፣ የማማረር ወይም የመሰላቸት ስሜት አይታይባቸውም። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ትህትናቸው! እነዚህ ወጣቶች እየተከተሉት ያለው ከፍተኛ የሙያ ስነምግባርና የስራ ፍቅር እጅግ የሚደነቅ ነው። ከተመረቁ በኋላ በዚሁ መነሳሳት ከቀጠሉ፣ በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የህክምና ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ ተማሪዎችም በዚህ አይነት ስነምግባርና የስራ ፍቅር ከተገነቡ፣ በኢትዮጵያ የህክምና አገልግሎት ውስጥ ያለው የስራ ባህል ያለ ጥርጥር ይቀየራል።

በወጣቶቹ ስነምግባርና የስራ ጉጉት ከመገረሜ የተነሳ ከአንድ ወር በፊት፣ ለአንድ ከኢንተረኔት ካፌ ውስጥ ለተዋወኩት የሁለተኛ ደረጃ መምህር በጨዋታችን መካከል አነሳሁለት። "ሲመረቁና ስራ ሲመደቡ ሁሉም ቦታውን ይይዛል" በማለት በእጩዎቹ ሀኪሞች ላይ የለውጥ ተስፋ እንደማይታየው ገለፀልኝ። በመንግስት ተቋማት በሚሰጡ አገልግሎቶች እርካታ የተነፈገ ህዝብ፣ የለውጥ ጭላንጭል አልታይህ ቢለው አይፈረድበትም።

ስለነገዎቹ የህክምና ባለሙያዎች ብዙ መልካም ነገር ማውሳቴ፣ እነሰም-አደገም የሚማሩበት ዩኒቨርሲቲ መምህር ነኝና ይህን በማወቃቸው በመጠኑም ቢሆን ለየት ያለ እንክብካቤ ወይም አገልግሎት ስለአገኘሁ አይደለም ይህን ሁሉ የምስክርነት ቃል የሰጠሁት። በሁለቱም ጊዜ ቆይታዬ፣ የማስታምማቸው ሰዎች ህክምናቸውን ጨርሰው ሊወጡ አካባቢ ነው የዩኒቨርሲቲው መምህር መሆኔን ባጋጣሚ አንድ-ሁለት ተማሪዎች ያወቁት።

## የህሙማን መኝታ ክፍሎች

የህሙማን ተኝቶ መታከሚያ ክፍሎች ብዙ ብዙ ችግሮች አሉባቸው። ከሁሉም አንገብጋቢው ችግራቸው ግን የቁጥራቸው ማነስ ነው። ሆስፒታሉ ችግሩን እየተፈታ ያለው በሁለት መንገድ ነው። አንደኛ፣ አንድ የህሙማን ክፍል መያዝ ከሚገባው የአልጋ ቁጥር በላይ እንዲይዝ በማድረግ፤ ለምሳሌ አራት አልጋዎች መያዝ ያለበት ክፍል አምስት ወይም ስድስት አልጋዎች እንዲይዝ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# እኛ እንዲህ እንላለን (ሶስት)

# የስልታዊ ዕቅድ (ስትራቴጂክ ፕላን) ዝግጅት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል

አበባው ይርጋ አዳሙ (ዶ/ር)
ትምህርትና ስነባህርይ ፋኩልቲ

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘመናዊ (የአውሮፓውያን አይነት) የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተጀመረው እ.ኤ.አ በ1950 ነው፡፡ እንደ እ.ኤ.አ. እስከ 1985 ድረስ አርባ አንድ ሚሊዮን ለሚጠጋ ህዝብ ኢትዮጵያ ያላት አንድ ዩኒቨርሲቲ ብቻ ነበር - አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ እ.ኤ.አ. በ1985 የአለማያ እርሻ ኮሌጅ ወደ አለማያ ዩኒቨርሲቲ (አሁን ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ) በማደጉ በሀገሪቱ ያለው የዩኒቨርሲቲ ብዛት ወደ ሁለት ከፍ ብሏል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መስፋፋት ቀጥሎ እ.ኤ.አ. ከ1999-2005 ባሉት ዓመታት ውስጥ የተለያዩ ኮሌጆችንና ተቋማትን (institutes) በማዋሃድና ወይም በማሳደግ ስምንት ተጨማሪ ዩኒቨርሲቲዎች ተከፍተዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር የቀድሞዎቹ የባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅና የባሕር ዳር ፖሊቴክኒክ ተቋምም ተዋህደው የአሁኑ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተመሰረተው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተቋቋመበትን ዓላማዎች ለማሳካት የተለያዩ ዕቅዶችን ሲያወጣና ሲተገብር ቆይቷል፡፡ ይህ በተጠናከረ ሁኔታ ቀጥሎ ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት፣ ማህበረሰቡን በከፍተኛ ደረጃ ለማገልገልና በአህጉሩ ከሚገኙ “አስር ምርጥ የምርምር ተቋሞች አንዱ” ለመሆን ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲው እነዚህን ዓላማዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለማሳካት እንደግብዓትና አቅጣጫ መጠቆሚያነት ከሚጠቀምባቸው ዋነኛ መሳሪያዎች አንዱ ስትራቴጂክ ፕላን ነው፡፡ የዚህ ጽሁፋችን ዋነኛ ዓላማም ከስትራቴጂክ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ጋር የተያያዙ ሃሳቦችን በማንሳት ዩኒቨርሲቲው ቀጣይ የሚያዘጋጀው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ፕላን የተሻለ እንዲሆን ማገዝ ነው፡፡
እኛ እንዲህ ስንል የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና የሚመለከታቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላትም በጉዳዩ ላይ ጥልቅ ውይይት በማድረግ እንዲያ ይላሉ ብለን እናስባለን፡፡ የስትራቴጂክ ፕላኑን ለማዘጋጀት ኃላፊነት የሚሰጠው ቡድንም የሚቀርቡ ሃሳቦችን በቅንነትና በሁለትም አይኑ አይቶ ዩኒቨርሲቲው በመማር ማስተማሩ፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት በቀጣይ አምስት አመታት የላቀ ውጤት እንዲያስመዘግብ የሚያግዝ ስራ ይሰራል ብለን እናምናለን፤ አምነንም እንዲህ እንላለን፡፡


ስትራቴጂክ ፕላን አንድ ተቋም አሳካቸዋለሁ ብሎ የሚያስባቸውን ዓላማዎች ለመተግበር ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ ሊታቀድ ይችላል፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም ዓላማዎቹን ተግባራዊ ለማድረግ ያግዘው ዘንድ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ፕላን ነድፎ ሲንቀሳቀስ ቆይቶ አሁን በዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት ላይ እንገኛለን፡፡ በመገባደድ ላይ የሚገኘው ስትራቴጂክ ፕላን የዩኒቨርሲቲውን ርዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶች መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ የየትኛውም ዩኒቨርሲቲ ርዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶች በዘፈቀደ የሚጻፉ፣ ግለሰቦች የሚፈልጓቸው ወይም ለታይታ ብቻ የሚቀርቡ መሆን እንደሌለባቸው እናምናለን፡፡ ይልቁንም ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅና በሌሎችም ሰነዶች የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር ለመወጣት የሚያስችሉ ዋና ዋና ምሰሶዎች ናቸው፡፡ ይህ ከሆነ የዩኒቨርሲቲው የቀጣይ አምስት ዓመታት ስትራቴጂክ ፕላን የተሻለ እንዲሆን ካለፈው ስትራቴጂክ ፕላን ምን እናሻሽል?

## በሁሉም ባለድርሻ አካላት ዘንድ የሚታወቅ እንዲሆን ጥረት ማድረግ

እ.ኤ.አ በ2012 የምርምር ስራ ከሚያደርጉ መምህራን መካከል የተወሰኑት የዩኒቨርሲቲውን ስትራቴጂክ ፕላን በመረጃ ምንጭነት ተጠቅመው ነበር፡፡ በወቅቱ ከኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ጽህፈት ቤት ያገኙት ይህ ሰነድ የዩኒቨርሲቲው ዋነኛ እሴቶች የሚከተሉት እንደሆኑ ያትታል፤ quality, Integrity, transparency, accountability, rule of law, equality, and promoting diversity (ምስል 1)፡፡ በወቅቱና አሁንም ጭምር እነዚህ ዋነኛ እሴቶች ከርዕይና ተልዕኮው ጋር በህብረ ቀለም አሸብርቀው በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተለጥፈው እናገኛቸዋለን፡፡

ከአንድ ዓመት በኋላ (እ.ኤ.አ በ2013) በተለያየ ቦታዎች ላይ ተለጥፈው ያየናቸው የዩኒቨርሲቲው ዋነኛ እሴቶች አብዛኞቹ ቀድሞ ከምናውቃቸው የተለዩ ሆነው አገኘናቸው፡፡ እነዚህ እሴቶች የሚከተሉት ናቸው፤ Qyality, Discourse, Innovation, Integrity, Democratic culture, and Social responsibility (ምስል 2)፡፡

ይህንን ጉዳይ ያጫወትናቸው ጓደኞቻችን በምስል 1 ላይ የቀረበው ረቂቅ፣ በምስል 2 ላይ የቀረበው ደግሞ ጸድቆ ስራ ላይ የዋለው ስትራቴጂክ ፕላን አካል ሊሆኑ እንደሚችሉ ግምታቸውን ነገሩኝ፡፡ እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን እናንሳ፡፡ አንደኛ፣ ስትራቴጂክ ፕላን የሚባለው በዕቅዱ ውስጥ ከሚካተቱት ዓመታት ውስጥ የመጀመሪያ የሚባለው ዓመት ከመጀመሩ በፊት ተዘጋጅቶ የሚጠናቀቅ ይመስለናል፡፡ ይህ ማለት ግን በሂደት የሚሻሻል ነገር የለም ማለት አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ የስትራቴጂክ ፕላን መተግበሪያ ዓመቱ ከተጀመረ በኋላ ይቀየራሉ ተብሎ ከማይጠበቁ ነገሮች አንዱ እሴቶች ናቸው፡፡ ከተቀየሩ ደግሞ የተሰጣቸውን ግምት የሚያቀል ከመሆኑ ባሻገር እቅዱ በቂ ትኩረት ወይም ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ ያልተከናወነ ነው ብሎ እንዲታሰብ ያስገድዳል፡፡ ሁለተኛ፣ የመጀመሪያው ረቂቅ ነው ብልን የምናስብ ከሆነ በትምህርትና




(ምስል 1)

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# እኛ እንዲህ እንላለን

ከገጽ 8 የዞረ




(ምስል 2)

ስነባህርይ ፋኩልቲ ዲን ጽህፈት ቤትና በሜዲካል ፋኩልቲ ዲን ጽህፈት ቤት በር ላይ አሁንም ድረስ የዩኒቨርሲቲው እሴቶች እነዚህ ናቸው ተብለው መለጠፋቸው ምን የሚሉት ነው? ይህ የሚያሳየው ስትራቴጂክ ፕላኑ በአንዳንድ ባለድርሻ አካላት ዘንድ በግልጽ የማይታወቅ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተፈጻሚነቱ ላይ ትልቅ ጥያቄ ያስነሳልና አንድ ሊባል ይገባል፡፡

በተጨማሪም ለአምስት ዓመት ተብሎ በተዘጋጀው ስትራቴጂክ ፕላን ላይ የሰፈሩት የዩኒቨርሲቲው ዋነኛ እሴቶች ምናልባትም ከአምስት ዓመት በላይ ተግባራዊ ሊሆኑ ሲገባ እንዴት በዓመት ውስጥ ሊቀየሩ ቻሉ? ማን ቀየራቸው? የአንድ ዩኒቨርሲቲ ዋነኛ እሴቶችን የሚያወጣና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚቀይራቸው ማን ነው? በየስንት ጊዜው? የስትራቴጂክ ጊዜው ሳያበቃ የእሴቶቹ መቀየር ቀድሞውንም ቢሆን በዘፈቀደ የተዘጋጁ ነበር ለማለት ያስደፍር ይሆን? ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚመለከታቸው ሰዎችና የዕቅድና ፕሮግራም ባለሙያዎች መልስ የሚሰጡበት ቢሆንም እኛ ግን የእነዚህ ዋነኛ እሴቶች መቀየር በስትራቴጂክ ፕላኑ ውስጥ ተግባራዊ ሊደረጉ የታቀዱ ጉዳዮችንስ በተወሰነ ደረጃ አያፋልስም ወይ ብለን እንጠይቃለን፤ መልስም እንጠብቃለን፡፡

እኛ የዩኒቨርሲቲው ኃላፊዎች፣ መምህራንና ሰራተኞች የዩኒቨርሲቲው ዋነኛ እሴቶችን ንገሩን ለሚለን ሰው አንድ አይነት መልስ እንሰጣለን ወይ ብለን ራሳችንንም እንጠይቃለን፡፡ ይህ ሳይሆን ቢቀር እንኳን በቀጣዩ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ፕላን ዝግጅት ወቅት መሰል ስህተቶች እንዳይፈጸሙ አደራ እንላለን፡፡

## “እቅድ ዶሮ ክንውን ሽሮ” እንዳይሆን እንጠንቀቅ

እየተገባደደ ባለው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ፕላን ውስጥ ቢተገበሩ የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሻለ እንዲሆን የሚያደርጉ፣ በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ መካከል መልካም ግንኙነት ለመፍጠር የሚያግዙ እንዲሁም ሌሎች በርካታ አዎንታዊ ለውጦችን ለማምጣት የሚያስችሉ ጉዳዮች በዕቅድ መልክ ተይዘውና አፈጻጸማቸውም ጊዜን መሰረት ባደረገ መልኩ ተዘርዝረው እናገኛለን፡፡ እዚህ ላይ እያንዳንዱን ጉዳይ አንስቶ መወያየቱ ከአቅምም ሆነ ከጽሁፉ ዓላማ አንጻር የሚያስኬድ አይሆንም፡፡

ይሁን እንጂ ሊሻሻሉ ይገባል የምንላቸው ጉዳዮች የሚያሳዩልንን የተወሰኑ አስረጅዎች ማቅርብ የግድ ይለናል፡፡ ይህን ስናነሳ ግን የታቀደ ሁሉ ይተገበራል ከሚል ግትር እሳቤ እንዳልሆነ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ከህይወትና ከስራ ልምዳችን እንዳየነው ይህ ሊሆን እንደማይችል እናውቃለንና፡፡ እዚህ ላይ የምናነሳው ዋናውና ትልቁ ጥያቄ ዩኒቨርሲቲው አቅሙ እያለውና ሁኔታዎች እየፈቀዱ ስለምን ነው ያቀደውን ሊተገብር ያልቻለው የሚለውን ነው፡፡ እየተገባደደ ባለው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ፕላን ውስጥ በዕቅድ የተያዙ እጅግ በርካታ ጉዳዮች ሳይተገበሩ ብቻ ሳይሆን ሊተገበሩም ሳይታሰቡ ካለፉት እጅግ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ይገኙበታል፤

(ሀ) developing a system that enables students to become individuals who have good ethical and social values and capable of respecting and promoting diversity, (ለ) developing and delivering courses on gender assertiveness and diversity to undergraduate students, (ሐ)organizing seminars or conferences or panel discussions on ethics, social values and diversity issues, and (መ) creating a sense of belongingness and a culture of participation and responsiveness, (ሰ) organizing major cultural events at institutional level.

እዚህ ጋር ለምን ብለን እንጠይቃለን፡፡ የሰው ኃይል ዕጥረት? የአፈጻጸም ብቃት ማነስ? ለጉዳዩ የተሰጠው ትኩረት ማነስ? ወይስ ምን? በስትራቴጂክ ፕላን ውስጥ የሚታቀዱ ጉዳዮች ሁሉ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንቶችት ካልሆነ በስተቀር በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መተግበር አለባቸው ብሎ ከሚያምን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንዲህ አይነት ድክመት የሚጠበቅ አይደለም፡፡

ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው በተግባር ሊፈጽም የማይፈልጋቸውን ወይም በተለያዩ ምክንያቶች በስትራቴጂክ ፕላኑ የስራ ጊዜ ውስጥ ሊተገበሩ የማይችሉ ጉዳዮችን ለዕቅድነት ብቻ አለያም ለስትራቴጂክ ፕላንና ለሪፖርት ማሳመሪያነት ሲባል ብቻ ባያስገባ መልካም ነው ብለን እናስባለን፡፡ ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነት አካሄዶች ሲበረክቱ ፈጻሚና የዕቅዱ ተጠቃሚ አካላት “ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ” ስለሚሉ ለስትራቴጂክ ፕላኑ የሚሰጡት ትኩረትም ሆነ በእሱ መሰረት የመመራት ፍላጎታቸው እየቀነሰ ይመጣል፡፡ ይህ ደግሞ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በዩኒቨርሲቲው ላይ ያላቸውን እምነት ይቀንሳል፤ ያለዕቅድ የሚመራ የተማረ ማህበረሰብንም ይፈጥራል፤ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ተቋማዊ ጥንካሬን ይሸረሽራል፡፡

## አጠቃሎ - እና ምን ይደረግ?

በስትራቴጂክ ፕላን ዝግጅት ላይ የጠለቀ እውቀት ባይኖረንም ከትንሽ ንባብና ከተሞክሯችን በመነሳት እኛ እንዲህ እንላለን፡፡ 1) በቅድሚያ የዩኒቨርሲቲው አመራር ቦርድና ኃላፊዎች ስትራቴጂክ ፕላን ዩኒቨርሲቲው አዎንታዊ ለውጥ እንዲያመጣና ከፍተኛ ዕድገት እንዲያሳይ ለማድረግ የሚያገለግል ዓይነተኛ መሳሪያ እንደሆነ በሚገባ ሊረዱና ለተግባራዊነቱም አጥብቀው ሊሰሩ ይገባል፡፡ 2) ጥሩ የስትራቴጂክ ፕላን ዝግጅት የቀደሙ ተሞክሮዎች መለስ ብሎ ማየትንና የሁሉንም ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ከባለፈው ስትራቴጂክ ፕላን ምን ተረዳን (ድክመት/ጥንካሬ - በዕቅድና አተገባበር) ብሎ መጠየቅና ባለድርሻ አካላት በተለያየ መልኩ በዝግጅቱ ላይ ጠንካራ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ 3) በስትራቴጂክ ፕላኑ ውስጥ ሊተገበሩ የሚታቀዱ ጉዳዮች በሙሉ እንዲያው ለይስሙላ (ለላንቲካ) ወይም ለማሽብረቂያና ሪፖርታዊ ግዴታን ለመወጫ መሆን የለባቸውም፡፡ በመሆኑም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መሰረት የሚተገበሩና የታሰበውን ውጤት ለማምጣት የሚያግዙ መሆናቸው ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡ 4) የተለያዩ ዕቅዶችን የሚተገብሩ አካላት/ክፍሎች በግልጽ ሊቀመጡ እንዲሁም ተፈጻሚነታቸውን የሚቆጣጠርና የሚገመግም አካል ሊኖር ይገባል፡፡ 5) ፈጻሚውም ሆነ አስፈጻሚው አካል ሙሉ ኃላፊነት ሊሰጠውና ተጠያቂነት እንዳለበት ሊያውቅ ይገባል፡፡ 6) በተግባር ላይ የሚውለውን ስትራቴጂክ ፕላን ባለድርሻ አካላት ሁሉ ሊያውቁትና የስራቸው መቃኛ ሊያደርጉት ይገባል፡፡ ቸር እንሰንብት፡፡

## አባባሎች

በሙሉጎጃም አንዱአለም

ፀፀትና ተረከዝ ከወደኋላ ይከተላሉ፡፡

ሽማግሌ ደህና ነኝ፣ ነጋዴ አተረፍኩ አይልም፡፡

የእንጀራ እናት የእንጀራ ልጇን የጐሪጥ እያያያች ወተት ትደፋለች፡፡

# ፈለገ ህይወት ሆስፒታል ...

ከገጽ 11 የዞረ

## የሞባይል ቀበኞች

ለአንድ ተኝቶ የሚታከም ሰው በአስታማሚነት አብሮ መዋልና ማደር ያለበት ሰው አንድ ቢሆንም፣ በርካታ አስታማሚዎች ይህን መርህ አይከተሉም፡፡ ሁለትም-ሶስትም ሆነው ከሆስፒታሉ ያድራሉ፤ ላስታማሚዎች ይቅርና ለታካሚዎች የአልጋ የመኝታ ክፍል ከፍተኛ እጥረት ያለበት ሆስፒታል ነውና አንዳንዶች ከህመምተኛው ጋር ተደርበው፣ አንዳንዶች ከወለሉ ላይ ካርቶን አንጥፈው፣ ሌሎች ደግሞ በዛፎች ስር ወይም ለታካሚዎች መቀመጫ እንዲሆኑ በተሰሩ አግዳሚ ወንበሮች ላይ ይተኛሉ፡፡

በዚህ መሀል የማይተኙ፣ አስታማሚ መስለው የሚገቡና እንቅልፍ ድብን አድርጎ ከወሰዳቸው አስታማሚዎች ወይም ታማሚዎች ሞባይል የሚሰርቁ፤ የሞባይል ቀበኞች አሉ፡፡ አንድ አስታማሚ የሚያስታምመውን ሰው ሌሊት ላይ ወደ መፀዳጃ ቤት ይዞ ከሄደም ቀበኞቹ ፈጠን ብለው በመግባት የታማሚውን አልጋ ይፈትሻሉ፤ በተለይ ከትራሱ አካባቢ - ብዙ ሰዎች ሲተኙ ሞባይላቸውን ከትራሳቸው ስር ስለሚያስቀምጡ፡፡ ባለፈው የካቲት ወር እኔ እያስታመምኩ ከነበርኩበት ክፍል የነበረ ታካሚና የአስታማሚው ስልክ የተሰረቀው በዚህ መንገድ ነው፡፡

## "አንድ ቢኒ..."

ከሆስፒታሉ ግቢ ውስጥ ያለው ካፌ በጣም ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ምግብ፣ ሻይና ቡና እንዲሁም ለስላሳና ሌሎች የታሸጉ መጠጦች ያቀርባል፡፡

አንድ ግን የታዘብኩት ነገር አለ፤ ጉዳዩ ከብርጭቆ አጠቃቀም ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ማንኛውም የውጭ ተጠቃሚ (አስታማሚ፣ ታካሚ ወይም ሁለቱም) ሻይ፣ በማሽን የተፈላ ቡና፣ ማኪያቶ ወይም የሚጠጣ ውሀ ካዘዘ፤ አስተናጋጆቹ በተለመደው መንገድ "አንድ ሻይ"፣ "አንድ ቡና" ወይም "አንድ ውሀ" በማለት ያዛሉ፡፡

ተስተናጋጁ የሆስፒታሉ ሀኪም ወይም ሰራተኛ ከሆነ/ችና ተመሳሳይ አገልግሎት ከጠየቀ/ች፣ አስተናጋጆቹ የሚያዙበት "ቋንቋ" በተወሰነ መልኩ፣ ሆኖም ትርጉም ባለው መንገድ ይቀየራል - ሻይ ካዘዘ "አንድ ቢኒ ሻይ"፣ ቡና ካዘዘ "አንድ ቢኒ ቡና"፣ ውሀ ካዘዘ "አንድ ቢኒ ውሀ" በማለት ያዛሉ፡፡ ስለሆነም የሚጠጣው ነገር (ሻይ፣ ቡና፣ ውሀ) በተለየ ብርጭቆ ውስጥ ሆኖ ይቀርባል፡፡ እናም "ቢኒ" የሚጠጡ ነገሮችን በተለየ ብርጭቆ ለሆስፒታሉ ሰራተኞች ለማቅረብ "የተፈጠረ" 'የሚስጥር ቃል' (ኮድ) ነው ማለት ነው፡፡ ባለፈው አመት ዘመድ ሳስታምም በነበረበት ወቅት አገልግሎት ላይ የነበረው ኮድ "ስታፍ" የሚል እንደ ነበር አስታውሳለሁ -"አንድ ስታፍ ሻይ"፣ "አንድ ስታፍ ቡና"፣ "አንድ ስታፍ ውሀ"፡፡ ዘንድሮ "ቢኒ" በሚል ቃል ተቀይሯል፡፡

ስለሆነም የኮድ ስርአቱ ታስቦበት የተፈጠረ ነው ማለት ነው - ሌላው ወይም "ተራው" ሰው በሚጠቀምበት እቃ ላለመጠቀም እናም ምናልባትም ሊያጋጥም ከሚችል ተላላፊ በሽታ ራስን ለማዳን፡፡ ሆኖም አድሏዊ የመሰለ የኮድ ስርአት ከመዘርጋት ይልቅ፣ የህክምና ባለሙያዎች ባሉበት የጤና ተቋም ውስጥ የሚገኙ የካፌ ሰራተኞችን መሰረታዊ የንፅህና አጠባበቅ ዘዴን በማስተማር ችግሩን ከስሩ መፍታት አይበልጥም ነበር?

## አይሞላልሽ ባተሌ

እርግጥ ነው - የሆስፒታሉ የአገልግሎት አሰጣጥ በብዙ መንገድ ተሻሽሏል፡፡ የካርድ ክፍል ሰራተኞች ያላቸው ትብብርና ትህትና በጣም የሚያስመሰግን ነው፡፡ "ከውጭ መድሀኒት ግዙ" መባል ቀርቷል፣ ወይም በእጅጉ ቀንሷል፡፡ ተኝቶ የሚታከምን ሰው ለመጠየቅ የነበረው መጉላላት ተስተካክሏል፡፡ ሆኖም ግን ከፍተኛ የሆነ የአልጋ ክፍል እጥረት አለ፤ በረንዳ ላይ ተኝተው የሚታከሙ ህሙማን አሁንም አሉ፡፡ የህክምና መሳሪያዎች እጥረት አሁንም አለ፡፡ በየህክምና ክፍሉ ያለው ወረፋ ያስመርራል፡፡ የሆስፒታሉን አገልግሎት የሚፈልጉ ታካሚዎች ቁጥርና የህክምና ባለሙያዎች ቁጥር እጅግ ያልተመጣጠነ በመሆኑ "የደንበኞች እርካታ አለ" ለማለት ያስቸግራል፡፡ ከዚህ በፊት የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር የነበሩት ዶ/ር መርአዊ አራጋው፣ ሀምሌ 2000 ሆስፒታሉ ባሳተመው መፅሄት ላይ በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ እንዲህ በማለት ነበር የሆስፒታሉን የባለሙያ እጥረት የገለፁት፤ "ያሉን ባለሙያዎች... አንድ ኩንታል ጤፍ ውስጥ የበተንካቸው ግማሽ ኪሎ የበቆሎ ፍሬዎች ናቸው፡፡"

ሌላው የሆስፒታሉ ዋና ችግር አገልግሎቱን፣ በብቃትና በተቀላጠፈ መንገድ እንዲሁም በብዛትና በጥራት ለመስጠት የሚያስችል ህንፃ የሌለው መሆኑ ነው፡፡ በሆስፒታሉ ውስጥ ብዙ ለውጥ፣ ብዙ ጥረት ቢኖርም ሆስፒታሉ አይሞላልሽ ባተሌ ከመሆን አልዘለለም፡፡ የአማራ ክልልን የጤናና የልማት ስራዎች በበላይነት ሲመሩ የነበሩ ትላልቅ ሀላፊዎች ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው ወይም የህይወት ታሪካቸውን ሲፅፉ "ሳልሰራው በመቅረቴ ይቆጨኛል" በማለት ከሚጠቅሱት ጉዳይ ውስጥ ፈለገ ሕይወት ሆስፒታልን የዘመናዊ ህንፃ ባለቤት ሳያደርጉ መቅረታቸው እንደሚሆን እገምታለሁ፡፡

የፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል በአሁኑ ሰአት አዲስ ዘመናዊ ትልቅ ህንፃ እየተገነባለት ነው - በግቢው ውስጥ በስተሰሜን በኩል፡፡ ይህ ህንፃ ሲጠናቀቅና ለአገልግሎት ሆስፒታሉን ተብትበው ከያዙት የመሰረታዊ ልማት ችግሮች ማለትም ከህክምናና ከመኝታ ክፍሎች፣ ከዘመናዊ የህክምና መሳሪያዎች፣ ከመፀዳጃ ቤቶችና ከመሳሰሉት ችግሮች ያላቅቀው ይሆን? በተስፋ እንጠብቅ፡፡

## የሰው ክብደቱ

የሰው ክብደቱ መለኪያው ለማንነቱ፣
በእድሜውም አይደል በሽበቱ፣
በስጋውም አይሆን በውፍረቱ፣
በሀብቱም አይደል በማካበቱ፣
ለክብደቱ መመዘኛው ለማንነቱ፣
በስነ ምግባሩ እና በስነስርዓት አዋቂነቱ፣
ከሙስና እና ከጠባብነት እርቆ መገኘቱ፣
እነዚህ ናቸው መለያዎቹ ለክብደቱ፡፡
በተጨማሪም አወቆ የማሳወቁ እና ሰርቶ የማሰራት ችሎታ ነው፣
እኔ አዋቂ ነኝ የማይል አለማወቁን የማወቅ ችሎታው ነው፣
ተምሮ የማስተማር እና ሰርቶ ማሰራት ችሎታው ሲኖረው ነው፡፡
እነዚህን ሲያሟሉ ነው ከባድ ሰዎች የምንላቸው፣
እነዚህን ካላሟሉ ነው ከባድ ሰዎች የምንላቸው፣
እነዚህን ካላሟሉ በሰውነታቸው ብቻ ሰዎች እንበላቸው፡፡
እኔስ ማነኝ ከአዋቂዎች ከከባድ ሰዎች ጋር ብመደብ ደስ ባለኝ፣?
መምህር አይደለሁም እማራለሁ ተማሪ ነኝ፡፡
ተምሮ አስተማሪ ተእግቶ የያተጋ፣
ሰለቸኝ የማይል እውነተኛ ዜጋ፣
ጊዜ የማይገድል ሲያማና ሲያወጋ፡፡

ከ፲ አ. ሞላ መስፍን የባሕር ዳር ነዋሪ 23/06/07 ዓ.ም

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን የተለያዩ ጹህፎች ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# ፈለገ ህይወት ሆስፒታል ...

ከገጽ 7 የዞረ

በማድረግ፡፡ ሁለት፣ በየመተላለፊያው (ኮሪደሮች) ላይ አልጋዎችን በማስቀመጥ ህሙማኑን እንዲተኙ በማድረግ፡፡

የመኝታ ክፍሎቹ በአሰራራቸው ኋላ-ቀር መሆናቸው ደግሞ ሌላው ችግራቸው ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የውስጥ መፀዳጃም ሆነ የመታጠቢያ ክፍል የላቸውም፡፡ ይህ ደግሞ በህሙማኑ ላይ ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል፡፡ ለመፀዳዳት ሲፈልጉ፣ የተተከለላቸውን የምግብ መርፌ ወይም የተጨማሪ ደም መስጫ እቃ በመያዝና በአስታማሚዎቻቸው በመደገፍ ወደ ውጭ መፀዳጃ ቤት መሄድ አለባቸው፡፡ ያን ያህል መሄድ ያልቻሉ ደግሞ በአስታማሚዎቻቸው ጋቢ ወይም ሌላ ጨርቅ እየተጋረደላቸው አምስት ወይም ከዚያ በላይ ታካሚዎችና የዚያኑ ያህል ብዛት ያላቸው አስታማሚዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ ለመፀዳዳት ይገደዳሉ፡፡

ሰውነትን (ገላን) የመታጠብ ጉዳይ ግን ከናንካቴው የተረሳ ነው፤ "የአካል ንፅህና ለታመመ ሰው አያስፈልገውም" የተባለ ይመስል፡፡ የውጭ መፀዳጃ ቤቶቹ (ሌላውን ችግራቸውን የምመለስበት ሆኖ) የመታጠቢያ ክፍል የላቸውም፡፡ ይህም በመሆኑ ህሙማኑ - በተለይም በአንፃሩ ረዘም ላለ ጊዜ በሆስፒታሉ የሚቆዩት - ሊታጠቡ የሚችሉበት እድል የላቸውም፡፡ አንዳንድ አስታማሚዎች - በተለይም ከገጠር የመጡት - ከመፀዳጃ ቤቶች አካባቢ ለልብስ ማጠቢያ ከተሰራና ምንም መከለያ ከሌለው ገንዳ ላይ በመውጣት ገላቸውን ሲታጠቡ አይቻለሁ፡፡

ሌላው ከህሙማን መኝታ ክፍሎች ጥበት የሚመጣው ችግር መታፈግ ነው፡፡ ከሚገባቸው በላይ በማጠጋጋት ጭምር ህሙማን እንዲተኙ ሲደረግ፣ የህሙማኑ ብቻ ሳይሆን የአስታማሚዎችም ቁጥር ይጨምራል፡፡ ህሙማኑ ብቻ ሳይሆኑ ብዙዎቹ አስታማሚዎች እዚያው እክፍሉ ውስጥ ስለሚቆዩና ምግብ ጭምር ስለሚበሉ የክፍሉ ጠረን ይቀየራል፡፡ ህሙማን ሊጠይቁ የሚመጡ ሰዎችም በተመሳሳይ ሰአት፣ በብዛት ስለሚገቡ ክፍሎቹ ይታፈናሉ፡፡

ሆስፒታሉ የህሙማን መኝታ ክፍል ብቻ ሳይሆን፣ በአጠቃላይ የህክምናውን ስራና አገልግሎት በጥራትና በተቀላጠፈ መንገድ ለመስጠት ስር የሰደደ ችግር ያለበት መሆኑን ለመረዳት ግቢውን ዞር-ዞር ብሎ ማየት ብቻ በቂ ሊሆን ይችላል፡፡ እናም እስቲ ህንፃዎቹን እንቃኝ…

## የህንፃዎቹ ሁኔታ

ፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል ያሉት ህንፃዎችና ቤቶች አሰራራቸው ብቻ ሳይሆን አቀማመጣቸው፣ አቀማመጣቸው ብቻ ሳይሆን ዲዛይናቸው ቅጥ ያጣና የተዘበራረቀ ነው፡፡ ለዚህ አንዱና ዋናው ምክንያት የተጠቃሚው ቁጥር በጨመረና ሆስፒታሉ የሚጠበቅበት የአገልግሎት አድማስ እየሰፋ በመጣ ቁጥር የሚያጋጥመውን የክፍል ጥበት ወይም ችግር ለመፍታት ሲሉ፣ በየወቅቱ የነበሩ አመራሮች (ከሆስፒታሉ እስከ ክልሉ ጤና ቢሮ) ጥቃቅጥ የቤት ግንባታዎችን በመስራት ችግሩን ለማስወገድ ሳይሆን ለማስታገስ መሞከራቸው ሳይሆን አይቀርም፤ በህክምና አነጋገር ማደንዘዣ ወይም ማስታገሻ በመውጋት ችግሩን ለጊዜው ብቻ ማቃለላቸው፡፡

ለዚህ ደግሞ ምድር ላይ ካሉት ግንባታዎች ወይም ቤቶች የበለጠ ምስክር የለም፡፡ ለምሳሌ ወደ ስድስት የሚሆኑ የውጭ መፀዳጃ ቤቶች ያሉ ሲሆን፣ በተለያየ ጊዜ የተገነቡ ለመሆናቸው በግንባታ መሀንዲስ ማስመርመር አስፈላጊ አይደለም፤ "ቁመናቸው" በራሱ ጥሩ ምስክር ነውና፡፡ የመጨረሻው አዲሱ (ስድስተኛው) መፀዳጃ ቤት በዚህ አመት መጋቢት ላይ ገና እየተጠናቀቀ ነበር፡፡ የውሀ ማጠራቀሚያ ጋኖቹም ("ታንከሮች") እንዲሁ ምስክር ናቸው፡፡ ከሁሉም ትልቅ የሆነው ሶስተኛው ወይም አራተኛው የውሀ ማጠራቀሚያ ጋን ግንባታ በዚሁ ወር ውስጥ በመጠናቀቅ ላይ ነበር፡፡

አንዴ የተሰሩ የህክምና ክፍሎችም በነበሩበት ሁኔታ ላይቀጥሉ ይችላሉ፡፡ የውስጥ ግድግዳቸውን በማፍረስ ማስፋት ወይም መጀመሪያ ከተሰሩበት አላማ ውጭ መጠቀም ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ ለምሳሌ "የሴቶች" እየተባለ የሚጠራ ህንፃ አለ፤ ወደ ሰባት አካባቢ የህሙማን መኝታ ክፍሎች ያሉት፡፡ ከተሰራ ብዙ እድሜ ያላስቆጠረ መሆኑ ያስታውቃል፡፡ በየአልጋው አንፃር፣ ከግድግዳው ላይ የተለጠፈው የእንግሊዝኛ ፅሁፍ፣ "የሴቶች ተኝቶ መታከሚያ፣ አልጋ ቁጥር…" (Female Medical Ward, Bed No…) የሚል ቢሆንም፣ አልጋዎቹ ለወንዶችም ጭምር አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

የሆስፒታሉ መሪዎች በተለያየ ጊዜ የወሰዱት እርምጃ በግራም-በቀኝም፣ በፊትም-በኋላም የተለያዩ ክፍሎች ያሏቸው ቤቶችን በመስራት ሆስፒታሉ ያሉትን የህክምናና የአስተዳደር ክፍሎች መሬት-ለመሬት በመለጠጥ ችግሩን ለማስታገስ መሞከር ነው፡፡ ከጥቃቅኖቹ ግንባታዎች "ግንባር" ላይ ተፅፎ የሚነበበውና መሬት ላይ ያለው ሀቅ የሚናገረው ይህንን ነው፡፡

እውነት-እውነቱን እናውራ ካልን፣ ከሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ቆሞ ዙሪያውን ለሚቃኝ እንግዳ ተመልካች ሆስፒታሉ በጨረቃ ቤቶች ግንባት የተወረረ ሊመስለው ይችላል፡፡ በውል እንዲታየው ቅርብ አካባቢ ካለ ህንፃ ሶስተኛ ፎቅ ላይ ሆኖ ሆስፒታሉን ወደ ታች ላየ ሰው፣ የህንፃዎቹ አቀማመጥ እጅግ ቅጥ ያጣ ከመሆኑ የተነሳ፣ አንድ የአርክቴክቸር መምህር ለመጀመሪያ አመት ተማሪዎች ምንም አይነት ትምህርት ሳይሰጥ የተለያዩ ክፍሎች ያሏቸው ቤቶችን ንድፍ እንዲሰሩ ካደረገ በኋላ፣ የሁሉንም ተማሪዎች የቤቶች ንድፍ በአንድ ላይ በመደርደር ያስቀመጠበት ጠረጴዛ ሊመስለው ይችላል፡፡

## የማዋለጃ ህንፃ

በፈለገ ህይወት ሆስፒታል ውስጥ ደረጃውን የጠበቀ ግንባታ ያለው በግቢው ውስጥ በስተደቡብ አቅጣጫ በኩል ነው፤ ህንፃው የማዋለድ አገልግሎት የሚሰጥበት ሲሆን እጅግ ዘመናዊ ባለሁለት ፎቅ ነው፡፡ የህንፃው ዲዛይን፣ የስራው ጥራትና በውስጡ ያለው "ፋሲሊቲ" እጅግ ደረጃውን የጠበቀ ነው፡፡ የመፀዳጃ ቤቶቹን ለአብነት ያህል ማየት ይቻላል፡፡ በየህሙማኑ/ወላዶች ክፍል ውስጥ ያሉ በመሆናቸው፣ ያለመሳቀቅና ወደ ሌላ ቦታ ወይም ክፍል ርቀው መሄድ ሳያስፈልጋቸው መጠቀም ይችላሉ፡፡ የመፀዳጃ ቤቶቹ መቀመጫዎች በጣም ከመዘመናቸው የተነሳ "ሴንሰር" የተከጠመላቸው በመሆኑ፣ አንድ ሰው ከተጠቀመ በኋላ ራሳቸው ናቸው ውሀ የሚለቁት/የሚደፉት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመፀዳጃ ክፍሎቹ የእጅና የገላ መታጠቢያዎችም ስላሏቸው የታካሚዎችንና ያስታማሚዎችን ጤንነትና ምቾት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ባጭሩ በዚህ የማዋለጃ ህንፃና በሌሎቹ የፈለገ ህይወት ሆስፒታል ህንፃዎች መካከል ያለው ንፅፅር የሰማይና የምድር ያህል ነው፡፡

ይህ ዘመናዊ ህንፃ ያለበት ችግር አንድ ነው፤ የተጠቃሚው ቁጥር እጅግ በመጨመሩ በመተላለፊያዎች ላይ የሚተኙ ወላዶች አሉ - አምናም ሆነ ዘንድሮ እንዳየሁት፡፡

## የመፀዳጃ ቤቶች አሰራርና ያሉበት ሁኔታ

ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የማዋላጃ ህንፃ ውስጥ ካሉት መፀዳጃ ክፍሎች በስተቀር፣ ሁሉም የሆስፒታሉ የመፀዳጃ ቤቶች የውጭ ናቸው፤ ዘመናዊም አይደሉም፡፡ እነዚህ መፀዳጃ ቤቶች በቁጥር አምስት ሲሆኑ፣ 34 ክፍሎች አሏቸው፡፡ ከ34ቱ የመፀዳጃ ክፍሎች መካከል፣ 18ቱ (ከግማሽ በላይ የሚሆኑት) አገልግሎት አይሰጡም፤ ለምን? ስለታሸጉ፡፡

ይህም በመሆኑ የመፀዳጃ ቤት ወረፋ፣ በሆስፒታሉ ውስጥ የተለመደ ትእይንት ነው፤ በቀንም ሆነ በማታ ወረፋ ሊኖር ይችላል፡፡ ንጋት ላይ ያለው ግን ለየት ያለ ነው፡፡ ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ተሰልፈው ይጠባበቃሉ - መፀዳጃ ቤቶቹ "የወንድ"፣ "የሴት" ተብለው ስላልተለዩ ሰልፉም ድብልቅ ነው - የወንድና የሴት፡፡ ከሆስፒታሉ መግቢያ በኩል ያለው መፀዳጃ ቤት ብቻ ነው - ተነቅሎ ግድግዳውን ከተደገፈ በር ላይ "የሴቶች ሽንት ቤት" የሚል ቃል ያለበት፡፡ ከጎን ያለው ግን "የወንዶች ሽንት ቤት" አይልም፡፡ በተዘዋሪ የወንድ መሆኑ እንዲታወቅ ይሆን "የወንድ" ያልተባለው?

ዋናው ነጥብ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የመፀዳጃ ክፍሎች "ለምን ታሸጉ?" የሚለው ነው፡፡ አንዱና ዋናው ችግር የአጠቃቀም ጉዳይ ነው፡፡ በተለያየ ቦታ ካሉ ሁለት የመፀዳጃ ቤቶች የውጭ ግድግዳ ላይ በጉልህ ከተፃፉት ማሳሰቢያዎች መካከል አንዱ እንዲህ ይላል፤

> "ከዚህ መፀዳጃ ቤት ተጠቅመው ሲጨርሱ ውሀ ይድፉበት፤
>
> ለሽንት ቤት መጠቀሚያ ድንጋይ፣ ቅጠልና ፔስታል ይዞ መግባት ክልክል ነው፤
>
> በአካባቢው ውሀና ሽንት መድፋት በጥብቅ የተከለከለ ነው፤
>
> ለአካባቢ ፅዳት ትኩረት እንስጥ!"

በርካታ የገጠር ሰዎች በሆስፒታሉ እየተኙ ስለሚታከሙ፣ በሽንት ቤት አጠቃቀል በኩል ችግር መኖሩን ባለፈው አመት ያናገርኳት የፅዳት ሰራተኛ እንዲህ ነበር ያለችኝ፤ "ከሽንት ፖፖው ላይ የብርቱካንና የሙዝ ልጣጭ በመጨመር ከሽንት ቤቱ ጉድጓድ ይደፉታል፡፡ ከዚያ ሽንት ቤቱ ይደፈናል፡፡"

ከመፀዳጃ ቤቶቹ አጠቃቀም ጋር ያለው ችግር ባጭሩ ይሄ ይመስላል፤ ቅጠል፣ ድንጋይ… የሚጠቀሙ አሉ፤ አላስፈላጊ ነገሮችን (የሙዝ፣ የብርቱካን ልጣጭ…) የሚጨምሩም አሉ፤ ከትክክለኛ ቦታው ውጭ የሚጠቀሙ አሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች ተደምረው የመፀዳጃ ቤቱን ቀዳዳ ይደፍኑታል፤ እናም መፀዳጃ ቤቱ አገልግሎት ከማይሰጥበት ደረጃ ላይ ይደርሳል፡፡ ታዲያ ለዚህ አይነቱ ችግር መፍትሄው ምንድነው? ማሳሰቢያ መፃፍ፣ እናም ዝም ማለት? አንዱ መፀዳጃ ክፍል ሲደፈን ዝም ማለት? ሁለተኛው ሲደገም ዝም ማለት? ሶስተኛውም ሲደገም ዝም ማለት? የተደፈነው መፀዳጃ ክፍል ሲበዛ መፀዳጃ ቤቱን ማሸግ? ከዚያ እንደ ገና አዲስ መገንባት፡፡ ለምሳሌ -ቀደም ሲል እንደ ተገለፀው - ባለፈው መጋቢት ወር አንድ አዲስ በመሰራት ላይ ያለ ተጨማሪ የመፀዳጃ ቤት በመጠናቀቅ ላይ ነበር፡፡ ግን ይሄ እንዴት መፍትሄ ሊሆን ይችላል? መፀዳጃ ቤት በተደፈነ ቁጥር፣ መፀዳጃ ቤት መገንባት መፍትሄ ሊሆን አይችልም - የሆስፒታሉን ግቢ ከማጣበብ በስተቀር፡፡

ሆስፒታሉ ያለበት የመፀዳጃ ቤት ችግር ያፈጠጠ-ያገጠጠ ችግር ከመሆኑ የተነሳ፣ በመፀዳጃ ቤቶቹ ዙሪያ ያለው ቦታ በሽንት ረስርሶ ማየት የተመደ ነገር ነው፡፡ ምሽት አካባቢ ላይ ወንዱም ሆነ ሴቱ ወይ ወደ አጥር ወይ ወደ አንዱ መፀዳጃ ቤት የውጭ ግድግዳ ጠጋ ብሎ ሲሸና ማየትም እንዲሁ የተለመደ ነው፡፡

ከመፀዳጃ ቤቶቹ አለመዘመን ባሻገር አንዱና ዋናው ችግር - ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው - የአጠቃቀም ችግር ነው፡፡ ይህን ችግር በቋሚነት ትምህርት በመስጠት ለመፍታት ለምን ጥረት አይደረግም? ማንኛውንም ተኝቶ ታካሚን ለሚያስታምም ሰው በቋሚነት የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም ስልጠና በመስጠት ችግርን ከስሩ ለማድረቅ ለምን አይሰራም? እንዴት የጤና ባለሙያዎች ሰራዊት ባለበት ሆስፒታል የጤና ጠንቅ የሆነ የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም ችግር ጎልቶ ይታያል?

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ናይል 3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4፣ ግንቦት 2007 ዓ.ም

# ID ዬ (ልቦለዳዊ ወግ)

በደስታ ተክስተ

ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የደህንነት አገልግሎት (BDU Security Service)

ስሜን አጥብቆ የሚጠይቀኝን ሰው አልወደውም፡፡ ውድ አንባቢዎች በእኔ ዘንድ ተወዳጅ ለመሆን ከፈለጋችሁ ስምህ ማን ነው? ብላችሁ እንዳትጠይቁኝ … ሌላም ማሳሰቢያ አለኝ ተማሪ መሆኔን ካወቃችሁ የምን? እና ስንተኛ አመት ተማሪ ነህም? ብላችሁ መጠየቅ አልፈቅድላችሁም ምክንያት አይጠቅማችሁምና፡፡ የመጣሁበትን ክልል ግን እነግራችኋለሁ የመጣሁት 10 ሲደመር 11 ከሚባል ቦታ ነው፡፡ ኧረ እባክህ የማነህ ፌዘኛ እንዲህ የሚባል የክልል ስያሜ በኢትዮጵያ ውስጥ የለም ልትሉኝ ትችሉ ይሆናል … አንባቢዎች እስቲ በመስማማት ይችን ወግ አንብባችሁ እስክታበቁ ድረስ ቢኖር ምን አለበት? አዎ ይኑር እንስማማ፡፡ መስማማት ይሻላል ከመተማማት ይል ነበር ጦር ሜዳ ሄዶ የሞተው አጐቴ፡፡

የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነኝና ID/መታወቂያ አለኝ ከፈለጋችሁ ቁጥሩን ልነግራችሁ 44ኛ ነው፡፡ መቼም እናንተ አንባቢያን ነገር በጥልቀት ስለምትመረምሩና አንዳንዶቻችሁም የቃላት ትራፊኮች ስለምትሆኑ ምን ነካህ አይ የፍሬሽ ነገር ፍሬሽ ፀሐፊ ስለሆን እንጂ … 44ኛ የሚል የወታደራዊ ክፈለ ጦር ስያሜ እንጂ የተማሪ ID/መታወቂያ አይደለም ሳትሉኝ አትቀሩም እና ለጊዜው የእኔ መለያ ቁጥር ይህ ነው … ቢሆን ምን አለበት? … ይሁን እንስማማ … መስማማት ይሻላል ከመተማማት ብሏልና አጐቴ… እናም ከተስማማን ወጌን ማስነበብ ልቀጥል፡፡

ከዕለታት በአንዱ ቀን ነው ከምሽቱ 5፡00 ሰዓት ገደማ ሆኗል የመኝታ ክፍል ተጋሪዎቼ ጨዋታ እንደቀጠለ ነው፤ አንዴ ስለፖለቲካ አንዴ ስለሐይማኖት ሲቀጥል ስለ ስፖርት ርዕሰ ጉዳዮች እየተነሳ ይፈጫል ይቦካል … ይጋገራል … እህል አይደለም ወሬ ሁሉም ተናጋሪ ሁሉም ተንታኝ ሁሉም አዋቂ ነኝ የበዛበት ዶርም፡፡ እኔ ግን አልጋዬ ላይ ጋደም እንዳልኩ በጆሮዬ የወሬውን ድምፅ ብሰማም ሃሳቤ ከእነርሱ ጋር አልነበረም፤ በራሴው የህይወት ምህዋር ዙሪያ ነበር የማጠነጥነው፡፡

… ገና ወደ ዩኒቨርሲቲ በገባሁበት እለት በአብዛኛው የበሶ ዱቄትና ስኳር የበዛበትን ሻንጣዬን በር ላይ ሳስፈትሽ … "ተማሪ ነህ ሲሉኝ" ጥበቃው አዎ አልኩት በድካም ስሜት "በል አይዲህን አሳየኝ" ሲለኝ እ..እ ስል ትንሽ ግር ብሎኝ ነበር ID የሚለው ቃል ማንነትን የሚገልጥ መታወቂያ መሆኑ ገብቶኝ ወዲያው የቀበሌ መታወቂያዬን ሳሳያቸው "ፍሬሽ ነህ" ሲለኝ አለገባኝም አልኩት ቃሉን ለመረዳት "ገና አዲስ ገቢ ነህ እንዴ" አለችኝ ወፍራሟ ሴት ጥበቃ…

ከቀናት ቆይታ በኋላ ነበር መደበኛ የዩኒቨርሲቲ መታወቂያ ተቀብዬ በግቢው ውስጥ በማንኛውም ቦታና ጊዜ ID ዬን ከኪሴ መለየት እንደሌለብኝ የተገነዘብኩት … እንደውም አንዱ ሲኒየር ተማሪ "ስማ የተሰጠህ መታወቂያ በምንም ሁኔታ ከእጅህ መውጣት የለበትም፡፡ በሆነ ምክንያት በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ አጥፍተህ ብትገኝ የካምፖስ ፖሊሶች ID ህን ይረከቡሃል፡፡ ከዚያም ተከስህ የዲሲፒሊን እርምጃ ይወሰድብሃል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ልትጫርም ትችላለህ …" ካለኝ ወዲህ የግቢያችንን ጥበቃዎች ሳያቸው መታወቂያዬን እንዳይወስዱብኝ እሰጋለሁ… በባህሪዬ ድንጉጥ ሰው ነኝና፡፡

በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ በርካታ ገጠመኞችን አስተናግጃለሁ፡፡ ከሁሉም ገጠመኞቼ መካከል ሳስበው ደስ የሚያሰኘኝ ቢኖር "ፍቅር ነው" "ምን ዓይነት ፍቅር?" እንዳትሉኝ "የሀገር ፍቅር ነዋ!" የምላችሁ መሰሏችሁ ከሆነ ተሸውዳችኋል፡፡ ገጠመኜ በሴት ፍቅር ላይ ያጠነጥናል፡፡ ፍቅረኛህ ማን ትባላለች? ብላችሁ እንዳት ጠይቁኝ አደራ በሰማይና በምድር ይሁንባችሁ፡፡ ስሟን ለማንም አላውስም ምክንያቱም ተውሶ የሚመልስልኝ ሰው ስለማይገጥመኝ ነው በእናንተስ ከአንባቢዎች ማንን አምናለሁ? … እኔ እኮ ምቀኛዬ ብዙ ነው፡፡ በእርሷ የተነሳ ብዙ አበሳ አይቻለሁ፡፡ በግቢያችን ካለው ላውጅ ከመጋበዝ ጀምሮ እስከ መንገድ ላይ የሚጠበስ ቸፕስና ሳምቡሳ መቀለብ የተማሪነት ኪሴን አራቁቻለሁ፡፡ ብዙ ዋጋ አስከፍላኛለች … ብዙ ኧረ ብዙ … ነው፡፡

በእርግጥ ከፍቅረኛዬ ጋር ስሆን ኪሴን የማይጠይቀኝ ጉዳይ ቢኖር ማታ ማታ በግቢያዎችን ውስጥ አንገት ለአንገት ተቃቅፈን ወክ/የእግር ጉዞ/ እናደርጋለን … ወካችንን በልተን ስንጠግብ ወደ አንዱ አትክልት ሥር ጨለማን ተገን አድርገን የፍቅር ጨዋታችንን እንኮመኩማለን አቤት ሲጥም … አዎን … ከቺኬ/ ከፍቅረኛዬ/ ጋር ሆነን የፍቅር ጨዋታችንን ስናቀልጥ የግቢ ፖሊሶች ድንገት በጨለማ ቦታ ተቃራኒ ፆታ ሆኖ መቀመጥ ክልክል ነው፡፡ ይሉንና ያስነሱናል፡፡ መቼም እንደ እድል ሆኖ ነው መሰል እኛን የሚገጥመን ጥቁር ፊት ያለው ጥበቃ ነው፡፡ የፍቅር ነገር የሚገባው አይመስለኝም አነጋገሩና ቁጣው ከፊት ገፅታው ጋር ተዳምሮ ያስፈራል፡፡ እኛም ታዲያ አይዲያችንን እንዳይቀማን እሺ ጋሼ በማለት ቶሎ በመነሳት ያው አንገት ለአንገት ተቃቅፈን ወካችንን እንሸከሽከዋል፡፡ ጐበዝ እስቲ ፍረዱን የት ሄደን የፍቅር ጥማታችንን እንወጣ ሰው እንዴት በገዛ ግቢውና በገዛ ገላው … "ተቃጠልን" አለች አሉ በርበሬ እሳት ላይ ሲጥዷት… ይሁን ብቻ ሁሉም ለበጐ ነው ይላል መፅሐፍ …

ይመስለኛል … እኔና ፍቅረኛዬ እንደተለመደው በምሽት ተቃቅፈን በግቢያችን ውስጥ የእግር ጉዞ ስናደርግ ቆይተን ድካም ስለተሰማን ማንም አያየንም ብለን በገመትነው ጨለማ ስፍራ ተቀምጠን የፍቅር ወሬአችንን መኮምኮም ጀምረናል፤ ምን ያህል ጊዜ እንደተቀመጥን አልታወቀንም ኮሽታ እንኳን በማይሰማማበት በዚያ ቀዝቃዛውን ምሽት በፍቅር መርከብ ላይ ወጥተን ደስ በሚለው የስሜት ማዕበል እንናወጣለን … ብቻ ምን አለፋችሁ … ገላ ለገላ ተጣብቀን ጭን ለጭን … ተቆላልፈን … ከንፈር ለከንፈር ተጣብቀን … በስሜት እሳት ተጥደን እየነደድን ባለንበት ሁኔታ … ድንገት … ያ … ፊተ ጥቁር የሆነ የካምፖስ ፖሊስ "ማነህ አንተ… እንዳትንቀሳቀስ" በማለት በአስፈሪ ድምፅ ሲጮህብን ከመደንገጣችን የተነሳ ነፍስ ከስጋችን ልትለይ ምንም ያህል አልቀራትም ነበር "ሰው ያለ ቀኑ አይሞትም" በሚለው እሳቤ ተረፍን እንጅ … "ምንድነው የምትሰሩት" እያለ ሲጠጋን እ…እ… እያጠናን ነው አልኩት በድንጋጤና በፍርሃት መንፈስ "ምንድነው የምታጠኑት?" በማለት ሲጠይቀን ዝም ስንለው "OK ተውት አውቀዋለሁ … Dark Live ነው አይደል? ለመሆኑ ይህን ኮርስ የሚሰጣችሁ መምህር ማን ይባላል?" ሲል ከተናገረ በኋላ በተናገረው ቃል እራሱ ከመጠን በላይ ይስቅ ጀምር … እኔና ፍቅረኛዬ በፍርሃት ይበልጥ ተቃቅፈን እናየው ጀመር ወዲያው … ጥቁር ፊቱን በጥቁር ጨለማው ውስጥ ይበልጥ ጠቁሮ ሲታየን … ጥርሱን ያጋጠጠ የሞት መላክ መስለኝ … በሉ ሁለታችሁም "ID አችሁን አምጡ" ሲለን እኔ እኔ … አይዲዮን አልያዝኩትም ዶርም ትቸው ነው የመጣሁት አለችው ፍቅረኛዬ … እየፈራች … "አንተስ?" ሲለኝ ጋሼ እ…እ…እ እኔ እያልኩ ሰርበተበት "ዝም ብለህ አምጣ ስጠኝ…." ከኋላ ኪሴ አውጥቼ ስዘረጋለት ከእጄ ላይ መንጥቆ ተቀበለኝና "የግቢውን መተዳደሪያ ደንብ አታውቁም አታነቡም እንዴ እንዲህ ያለ ነገር የዲስፕሊን እርምጃ ያስወስድባችኋል ለማንኛውም " አለና መታወቂያዬን ኪሱ አስገብቶ ሲሄድ …. እኔ ከኋላው እየተከተልኩ ጋሼ በናትህ የድሃ ልጅ ነኝ … እባክህ የዛሬን ID ዬን … ID ዬን… መልስልኝ ይቅረታ ጋሼ እያልኩ ስለምነው … አንተ አትከተለኝ ብየሃለሁ በማለት በእጁ የያዘውን ቆመጥ ሲቃጣብኝ እ…ኧረ …ኧረ ጋሼ በማሪያም … በመድሃኒዓለም … እያልኩ ወደ ኋላዬ ሳፈገፍግ ነበር ከተኛሁበት አልጋ ላይ ክፉኛ ስወድቅ ከወሰደኝ የእንቅልፍ ሰመመን የነቃሁት ከወደኩበት ወለል ላይ ስነሳ የድሮ ጓደኞቼ አይዞህ… አይዞህ… የሚል ድምፅና ሳቅ አጅቦኝ ነበር … ID ዬን … ማለቴን አስታውሳለሁ … በሉ አንባቢዎች ወጌን መልሱን አፌን …. አብሱ፡፡

እግዚአብሔር ኢትዮጵያ ሀገራችንን ይባረክ

ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን

- የተለያዩ ጹህፎች
- ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች
- የካርቱን ስእሎች
- ቀልድ
- ግጥም

እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወርዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# ምኞት (አጭር ልቦለድ)

በእንዳልካቸው ዘነበ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ተመራቂ ተማሪ

ዛሬ ከወትሮው ፈጠን ያለ እርምጃ እየተራመደ ነው፡፡ ምን እንደሆነ ለማወቅ ጓጓሁ ግን ምን ሳድርግ መጓጓት ብቻ ሆነ ከሉጫው ፀጉሩ ውስጥ ቀጠን ያለው ላብ ጠይም ፊቱን አልብሶታል፡፡ በመኖሪያ ቤታችን አጠገብ በወፍ ፍጥነት በሩጫ ሲያልፍ የሆነ ነገር ገመትኩ፡፡ ምን አልባት ሰዓት ረፍዶበት ይሆናል፡፡ አዎ አቤል ሰዓት ሲያረፍድ ብቻ ነው እንዲህ ዓይነት ሩጫ የሚሮጠው፡፡ ካልሆነማ እንደወትሮው በዝግታ እየተራመደ በሚያምር ድምፁ እየዘመረና እያፏጨ ነበር የሚያልፈው፡፡ ያኔ ታዲያ እንደልቤ እስኪበቃኝ ድምፁን ሰምቼ ጆሮዬን ከድምፁ ጥማት አረካው ነበር፡፡ አይኑንም አይቼ አይኖቼን ከናፍቆት እመልሳቸው ነበር፡፡

አቤል ጠይም፣ ፀጉሩ ሉጫ፣ አፍንጫው ጐረድ ብሎ ከፊቱ ውሀ ልክ ጋር ተባብሮ የተቀመጠ በተለይ ቁመናው በቃ ምን ልበላችሁ ወንዳወንድ ነገር ነው፡፡ ስለሱ ማሰብ ከጀመርኩ ወራት ተቆጠሩ አይኑን ካየሁበት ከዚያች ቅፅበት ጀምሮ ይሄው ለአራት ወራት እሱንና ስለሱ ብቻ ነው ማስበው፡፡ አቤልን እንዴት አድርጌ ማናገር እንዳለብኝ ሁሌም እንዳለመድኩት እያሰብኩ ነው፡፡ ምን ዋጋ አለው፤ አይደለም ፊቱ ቆሜ እንደምወደው ልነግረው ይቅርና ገና ተደብቄ ለማየው ፊቱ እንዴት ሰውነቴ በፍርሀት እንደሚወረር፡፡ በቃ ዛሬ ግን አልኩ የልቤን እነግረዋለሁ፡፡ ለምን ሲባል ነው በፍቅሩ ይህን ያህል የምሰቃየው? “አቤል ይ..ይ..ይቅርታ እኔን አታውቀኝም ግን…ግን..ግን… በቃ አፍቅሬሀለሁ” አቤት….ሲጨነቅ ከሄድኩበት የሀሳብ ባሕር የመነተፈኝ “አንቺ አጥር ጥግ ምን ይገትርሻል?” የሚለው የእናቴ ቁጣ አዘል ጥያቄ ነበር፡፡

እናቴን ረገምኳት፡፡ እንዴት ስለአቤል እያሰብኩ እንደዚህ ታስደነግጠኛለች፡፡ “በይ ተነሺና ቡኮው ኩፍ ያለ እንደሆነ አይተሽ አብሲት ጥለሽ እንጀራውን ጋግሪ” ሆ ጉድ እኮ ነው፡፡ ሰው በሰላም ሀገር እንደ እብድ ሰዓት ጠብቆ ከአጥር ስር ይቀመጣል እንዴ?” አለች እናቴ፡፡ ይህንን እንደ ተናገረች “ለቅሶ ቤት ልሄድ ነው፡፡” ብላኝ ወጣች፡፡ እኔ ግን ሁሉም ነገር አስጠልቶኛል፡፡ መብላት፣ መጠጣት፣ ማውራት፣ መስራት በቃ ምን ልበላችሁ ሁሉም ነገር ነው ያስጠላኝ….. የእናቴ ትዕዛዝ ቢያስጠላኝም እንኳ የግዴን መስራት አለብኝ ይህም ስለሁለት ምክንያት አንደኛው ስራዬን በጊዜ ጨርሼ የአቤልን መመለሻ ሰዓት ጠብቄ አይን አይኑን እያየሁ ፍቅሬን ለመግለፅ ሁለተኛው ደግሞ የእናቴን ትዕዛዝ በግድ ለመፈፀም፡፡

በፍጥነት ወደ ታዘዝኩት ሥራ አመራሁ፡፡ ቡኮውን ሳየው ኩፍ ብሏል፡፡ በፍጥነት እሳት አቀጣጥዬ አብሲት ጣልኩ፡፡ አብሲቱ እስኪደርስ የእንጀራውን ምድጃ ማስተካከሉን ተያያዝኩ ሁሉንም በመልክ በመልኩ አደረኩ፡፡

ምጣዴን አሰስኩ፤ የመጀመሪያውን እንጀራ ጋግሬ አወጣሁ ሁለት…. ሶስት….አራት….. አምስተኛው እንጀራ ነው መሰለኝ፡፡

ልክ እንዳሰፋሁት ማሰብ ጀመርኩ ግን አቤል ምን ይለኝ ይሆን? እውነት ፍቅሬን ይቀበለኝ ይሆን? ወይንስ ደግሞ የሴት ጓደኛ አለችው ይሆን?

> **ግን እንዴት እሳቱን የያዘውን ቀሚሴን በእጄ ልያዘው በፍጥነት መሬት ላይ ወድቄ በአፈሩ መተሻሸት ጀመርኩ…. ሙከራዬ ሁሉ አልሆነም እሳቱ ፀጉሬን ይዞታል ለመጨረሻ ጊዜ በሀይል ጮህኩና ሞቴን መጠበቅ ተያያዝኩ፡፡**

ብቻ ሁለቱም ሀሳቦች አስጠሉኝ፡፡ ስለ አቤል ሳስብ እየዋልኩ ባድር ደስ ይለኛል ዛሬማ የመጣው ይምጣ እናግረዋለሁ… አቤል ግን ፍቅረኛ ትኖረው ይሆን?… ኧረ በጭራሽ ራሴው ጠይቄ ራሴ መለስኩ ግን… በቃ ይኑረውም አይኑረው አቤል የኔ ብቻ ነው፡፡ ራስ ወዳድ ነሽ አልኩኝ ራሴን…. ከሄድኩበት ሀሳብ የመለሰኝ…. እንጀራው እንዳረረ ሲሸተኝ ነው፡፡ በፍጥነት አክንባሎውን አንስቼ እግሬ ስር ወረወርኩት፡፡ እንጀራውን አውጥቼ ትንሽ እንደቆየሁ እግሬን ሙቀት ሲሰማኝ ታወቀኝ፡፡ አክንባሎው በእሳት መያያዙን ሳላየው እግሮ ስር ወርውሬው ኖሯል ቀሚሴን ለበለበው፡፡ ቀሚሴ በእሳት ተያይዟል ደነገጥኩ፡፡ በፍጥነት ልሮጥ ስል ሊጡን በእግሬ ነክቼው ተደፋ፤ ወይኔ ምን አይነት አጋጣሚ ነው? እሳቱ ቀሚሴን፣ ባቴን አልፎ ወገቤን ሊያቃጥል እሳቱ ምንም አልቀረውም፡፡ ሮጥኩ ወዴት እንደምሮጥ አላውቅም በቃ….. መጮህ ጀመርኩ፡፡ ማንም አልሰማኝም፡፡ እኔ የምለው ከዚህ በፊት ከልክ በላይ ሳቃችሁ ብለው በር አንኳክተው ምን ተገኝቶ ነው? የሚሉን ጐረቤቶቻችን ዛሬ እኔ በእሳት ተቃጥዬ ስጮህ የማይደርሱልኝ ምን ሆነው ነው? ወይ እድሌ ሳስበው ማንም አይደርስልኝም፡፡ በቃ ቀሚሴን ለማውለቅ ቾኮልኩ፡፡ ግን እንዴት እሳቱን የያዘውን ቀሚሴን በእጄ ልያዘው በፍጥነት መሬት ላይ ወድቄ በአፈሩ መተሻሸት ጀመርኩ…. ሙከራዬ ሁሉ አልሆነም እሳቱ ፀጉሬን ይዞታል ለመጨረሻ ጊዜ በሀይል ጮህኩና ሞቴን መጠበቅ ተያያዝኩ፡፡ መሬት ላይ በምተኛበት ወቅት ከታች ሹል ድንጋይ አግኝቶኝ ኖሯል ከፀጉሬ አናት ስር ቀዝቃዛ ደም ሲፈስ ተሰማኝ፡፡ ኧረ ፈጣሪ ዛሬ ምን አይነት ቀን ነው?…. ቀኑን ረገምኩት… የማላውቀውን አቤልንም ጠላሁት፡፡ በሱ የተነሳ እኮ ነው እንደዚህ የምሆነው… “ኧረ ጌታ ሆይ ድረስልኝ፡፡ በእሱ ፍቅር ውስጤ አልቆ ከርሞ ዛሬ ደግሞ አካሌ በእሳት ይቃጠል፡፡”

በመጨረሻም ራሴን ትልቅ የመንግስት ሆስፒታል ውስጥ አገኘሁት፡፡ አይኖቼን በሰመመን ገልጬ ስመለከት በመጀመሪያ እናቴን አየሁዋት፣ በመቀጠል ዶክተሮችን አይኖቼን መልሼ ከመክደኔ በፊት ከኔ በስተቀኝ ማን እንዳለ ማየት ፈለግኩ፡፡ እጅግ በጣም እድሜ የጠገቡ የእናቴ የነፍስ አባት ቄስ እምሩ ናቸው፡፡ ብዙም አልገረመኝም፡፡ የአይኖቼን ሽፋሽፍት በመክደን ላይ እያለሁ በሩን ከፍቶ አንድ ወጣት ሲገባ አየሁ“አባ… ቅዳሴ ሰዓት ስለደረሰ እኔ ልሂድ” ሲል ተናገረ አይኔን ማመን አቃተኝ የኔው አቤል ነው፡፡ አይኖቼ እንባ አዘሉ፡፡ አቤል ግን ያውቃል ለሱ ስል እንደዚ እንደሆንኩ? “እሺ ልጄ ና እንጂ በሽተኛዋን እንኳን እግዚአብሄር አተረፈሽ” በላት «እሺ አባ» እንኳን እግዚአብሄር አተረፈሽ ብሎኝ እጄን ጨበጦኝ ወጣ… ደስ አለኝ.. ነፍሴ በሀሴት ተሞላች ስጋዬ በስቃይ! አቤልን ደግሜ ማፍቀር ጀመርኩ፡፡ በአገኘዋለሁ ተስፋ… ሕይወት እንደዚህ ነች….

---

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን

- የተለያዩ ጹህፎች
- ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች
- የካርቱን ስእሎች
- ቀልድ
- ግጥም

እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# ተረትና ምሳሌ በተረትና ምሳሌ ሲተረጐም

በሙሉጐጃም አንዱአለም

| መነሻው ተረትና ምሳሌ | ትርጉሙ |
|---|---|
| ካላዩት አይነድ ካልሰሙት አይቆጭ …………………… | ያላዩት አገር አይናፍቅም |
| ነብር ባየለበት ድመት ይኮርታል ……………………… | ንብ ሲነግስ ዝንብ ይነግስ |
| ሣይገድሉ ጐፈሬ ሳያዳምጡ ወሬ …………………… | አያገባው ገብቶ አያወዛው ተቀብቶ |
| | (አንበሳ ሣይገድሉ ቆዳውን ያስማማሉ) |
| መርፌ የራስዋን ቀዳዳ ሣትሰፋ የሰው ትጠቅማለች …… | የራስ ጉድ ጨለማ ነው |
| እጅግም ስለት ይቀዳል አፎት ………………………… | ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን |
| ሞኝ ቢመክሩት ከልማዱ አህያ ቢያጥቡት ከአመዱ …… | የለመደ ልማድ ያሰርቃል ከማድ |
| ጨረቃ ሲጠፋ ኮከብ አባወራ ይሆናል ………………… | ዋርካ በሌለበት ዋጮ አድባር ይሆናል |
| | (ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ) |
| ሰዶ ማሳደድ ቢያምርህ ደሮህን በቆቅ ለውጥ ………… | እውር ሲቀናጣ ዘንጉን ወርውሮ ፍለጋ ይሄዳል |
| ሰይጣን ሲያረምም በሀታዊ ይመስላል ………………… | እብድ ቢጨምት እስከ እኩለ ቀን ነው |
| ወፍ ጠባቂ ቢያደርጓት ድንጋይ ለቃሚ አገባች ………… | ትታጠቀው የሌላት ትኮናነበው አማራት |
| ተሹሞ የማይበላ ተጥዶ የማይፈላ ……………………. | ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል |

# ተረትና ምሳሌ

ፍርድ አያውቅ ዳኛ ተገን አያውቅ እረኛ

ሲሞቱ ገመድ ሲሾሙ ዘመድ አይታጣም

የድሃ መድሃኒቱ ጭንቀቱ

ብረት ካልፈላ አይላላ

እንግዳ ሣይመጣ ሁሉ ሴት

የሰው አገሩ ምግባሩ የከብት አገሩ ጌታው

በሰም የተጣበቀ ጥርስ ቢስቁበት አያደምቅ ቢበሉበት አያደቅ

ኮሶ ሲጠጣ ስግጥጥ ወተት ሲጠጣ ሽምጥ

ቁርበት ምን ያንጋጋሃል ቢሉት ባያድለኝ እንጅ የከበሮ ወንድም ነበርኩ አለ

ሞኝ ያገኘው ፈሊጥ ውሻ ያገኘው ሊጥ

አይናፋር ልጃገረድ ከወንድሟ ታረግዛለች

የደባ ገበያ በሬው በአስር ቆዳው በሃያ

በአጥንት የተመታ ውሻ አይጮህም

በሞኝ ክምር ዝንጀሮ ልጇን ትድር

አጥብቆ ጠያቂ የእናቱን ሞት ይረዳል

ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል

ትንሽ ቆሎ ይዘህ ከአሻሮ ተጠጋ

ከአራጅ ወዲያ ጐፈሬ አዝመራ የሣተው ገበሬ

አይጥም ጠላ ባል እና ሚስት ያጣላ

አይፅፍ ደብተራ ክንፍ የሌለው አሞራ

አድሎአዊ ዳኛ አምጡ ይላል የዶሮ ሻኛ

አገር በጤና ለማኝ በጭራ

አፍ ሲናገር አፍንጫ ያሽሟጥጣል

እህል ላበደረ አፈር ወርቅ ላበደረ ጠጠር

እህልን በጥቅምት ልጅን በጡት

እረኛ ቢያኮርፍ እራቱ ምሳ ይሆናል

እርሟን ብታፈላ ጋን ሙሉ አተላ

እሳት መጣልህ ቢሉት እሣር ውስጥ ገብቻለሁ አለ

እቤት ዶሮ ሲታረድ እዱር ቆቅ ይያዛል

እኔን የወደደ ከአንጀት ልጀን የወደደ ከአንገት

እንዴት ዋልሽ ለእናቱ ግንድ ለሚስቱ

እጭን ያለ ኮርቻውን እለምን ያለ ስልቻውን አያጣውም

ከመረቁ አውጡልኝ ከስጋው ፆመኛ ነኝ

ከመነኮሰች ባሰች ከቆረበች አፈረሰች

ከሚስቱ ጋር ያበረ ከእግዚአብሄር ጋር የተማከረ

ለፍቅር ብተኛት ለጠብ አረገዘች

በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ

በሚያዚያ ጐመን የዘራ ክረምቱን ሁሉ በላ

ባለቤት ካልጮኸ ጐረቤት አይረዳም

ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ

ልፋ ያለው በሐልሙ ዳውላ ይሸከማል

ባልንጀራው ቢያጠቃው ወደ ሚስቱ ሮጠ

ከጅብ ጅማት የተሰራ ክራር ድምፁ እንብላው እንብላው ይላል

ለሆዳም ሰው ማብላት ውቅያኖስን ለመደልደል መቃጣት ነው

ለመስራት ያፈረ ለመብላት ደፈረ

ለአሮጊት እማዬ፣ ለአገልጋይ እትዬ ብርቋ ነው

ለማዕበል ወደብ ለነፋስ ገደብ የለውም

ለጠላትህ እንደ ዳቦ እስኪገምጥህ አትመቸው

# <<ሳይቃጠል በቅጠል …

ከገጽ 16 የዞረ

የሚንጠባጠቡ ኢፈርቶችን መሰብሰብ የሚችል መዋቅር ቢሆን/ቢኖር ጥሩ ነው እላለሁ፡፡ የህይወት ክህሎት ጉይን በተመለከተ ተማሪዎችን መከታተል አለበት፡፡ ካውንስሊንግ እና ጋይዳንስ ክፍል ቢሰራ ተማሪው የራሱ ጥረት እያለ ዩኒቨርሲቲው ቢሰራ፡፡ የህይወት ክህሎት ስልጠና (life skills training) ሰጥተናቸው አሁን ሶስተኛ ዓመት የደረሱ ተማሪዎች አሉ፡፡ ተከታታይ ቲቶሪያል ቢሰጥ እላለሁ፡፡

ግዮን አለምሰገድ በሙሉዓለም የባህል ማዕከል የትወና ባለሙያ

በመጀመሪያ ይህን ችግር ከውስጥ ሁነሽ በማየት ከዝምታ ይልቅ ከተለያዩ የህብረተሰብ አካላት ጋር ተወያይተሽ መፍትሔ ለማግኘት የጀመርሽው መንገድ የጨዋ ኢትዮጵያዊ መገለጫ በመሆኑ ላመሰግንሽ እወዳለሁ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ባነሳሽው ጉዳይ ላይ ያለኝ አስተያየት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ለሚታየው ኢኮኖሚያዊም ሆነ ማህበራዊ ችግር የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ ያለበት ዩኒቨርሲቲው ለመሆኑ ጥያቄ አያሻውም፡፡ነገር ግን ህብረተሰቡም ጉዳዩን የአንድ ወገን ብቻ በማድረግ <<ጆሮ ዳባ ልበስ>>ብሎ መቀመጥ እንደሌለበት አምናለሁ፡፡

ስለዚህ በተቋሙ ውስጥ በመማር ላይ ያሉት ተማሪዎች ከማንኛውም ቦታ ይምጡ ነገ እችን ሀገር የሚረከቡ እህትና ወንድሞቻችን መሆናቸውን የማንክደው ሀቅ ነው፡፡ ስለዚህ <<ሳይቃጠል በቅጠል>>እንዲሉ የእነዚህን ወገኖቻችን ህይወት ለመታደግ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ከሚመለከታቸው የመንግስት|የግልና የተለያዩ ተቋማት ጋር ተቀራርቦ በጉዳዩ ላይ በመወያየት ፊታውራሪ ሁኖ መስራት እንዳለበት ይሰማኛል፡፡ በመጨረሻም እኔንና እኔን መሰል ኳደኞች በባህል ማዕከሉ በኩል በሙዚቃና ቲያትር ዝግጅት ገቢ ማሰባሰብ እንድንችል ዩኒቨርሲቲው ከባህል ማዕከሉ አመራሮች ጋር ተቀራርቦ ቢወያይ መልካም ነው እላሉ፡፡ አመሰግናለሁ

እርሶስ ምን ይላሉ? ይህ ጉዳይ ዛሬ ከእርሶና ከእኔ መልስ|እርምጃና ስራ ይጠይቃል;ይጠብቃልም፡፡ምን ያስባሉ?ነገ ደግሞ ቀጣዩን ትውልድ መልስ ጠባቂ ሆኖ እንዲቆይ ወይስ ዛሬ ላይ በጋራ እጅ ለእጅ ተያይዘን እንድንመልስለት እጅዎትን ሲልኩ? ከጥያቄ ጋራ ብሰናበትዎትስ?

ምስጋና - ለውድ የናይል ጋዜጣ አዘጋጆችና ለቃለ መጠይቁ ለተባበሩኝ

በሙሉ

# የግጥም ጥግ

## ማለት

ሀገር መውደድ ………… ማለት፣
ሀገር ሰው ስትፈልግ ሰው ሆኖ መገኘት፣
ማለት ………….፣
አፍቃሪ ነኝ ………….. ለማለት፣
ልክ እንደ ክርስቶስ፣
ዝቅ ብሎ ተገኝቶ ከፍ ብሎ መታየት፣
ማለት ……
አፍሪካዊ ነኝ …. ማለት
የጉጥ ቅርፊት ጥሶ፣
ጀግንነትን ወርሶ፣
ከብሄር ጥላ አልፎ፣
ጠባብ ካባን ገፎ፣
እሩቅ … አይቶ … ተሻጋሪ እልፍ አመታት፣
በላብ በወዝ … የራስ አድዋን መስራት
ማለት ….
•ተማርኩኝ … ምሁር ነኝ …. ማለት፣
እውቀትን .. መንዝሮ፣
ለትውልድ … አሻግሮ፣
ለወገኑ ችግር ለሀገሩ ብሶት፣
ፍቱን መድሃኒት ሆኖ ነው መገኘት፣
ማለት …
ኢትዮጵያዊ ነኝ … ለማለት፣ (በኩራት)
ድህነትን አሸንፎ በከፍታ ላይ መገኘት፡፡

ደስታ ተከስተ
BDU Security Service

## ጥሩ ስራ ስሩ

ሰው ቢሞት ቢቀበር አፈር ብትጫነው፣
መልካሙን ከሰራ ዘላለማዊ ነው፡፡
አሻራ አስቀምጦ እናቱን ያስጠራ፣
ሁልጊዜ ይኖራል ስለእርሱ ሲወራ፡፡
ስሙ ተመዝግቦ በታሪክ ማሕደር፣
ከትውልድ በትውልድ ለትውልድ ሲዘከር፣
በአለም ላይ ይነግሳል እንኳን በአንዲት መንደር፣
ጥሩ ስራ ሰሪ ዘላለም ይኖራል ስሙ ሳይቀበር፡፡
እናም ወዳጆቼ፣
እህት ወንድሞቼ፣
የትናንት አበቦች የነገ ፍሬዎች፡፡
ምሩቃን ምሩቃን ለሀገር ተጠሪዎች
ዘመንን ወገን ኢትዮጵያንም አኩሩ፣
በየምትሄዱበት ጥሩ ስራ ስሩ፡፡

ከጌታቸው እንደሻው

## እውነት

እውነት ሰይፍ ካልሆነ ጉልበት፣
ውሸት ከነገሰበት፣
ለእኔ ማለት ውሸት፣
ለእኔ ማለት እውነት፡፡
ሁለት አንድ ቅጠሎች፣
ሯሪ አልባ ፊደሎች!!

ውዱ ወርቁ

## ብቻ እድል ላግኝ

በአንቺ ተፈጥሬ ……. በአንቺ እኖራለሁ፣
ለአንቺ እዘምራለሁ …… ለአንቺ እታገላለሁ፣
ለአንቺ እቆስላለሁ …… ለአንቺ እደማለሁ፡፡
የሰርጌ ….. ደስታዬ፣
የለቅሶ ….. ሙሾዬ፡፡
ሁሉም በአንቺ ይሁን …. ሌላማ ምን አለኝ፣
እውነት ቃል ልግባልሽ …. ምን አለ እድል ኖሮኝ፡፡
ሕዝብን ተደግፌ ዙፋን ላይ ብወጣ፣
ከላብ ወዜ ውጭ …. የእጅ አመል ባመጣ፡፡
ለሰከንዶች እንኳን ሌላ አስቤ ብገኝ፣
እውነት .. እውነት .. ሀገሬ ኢትዮጵያ ስምሽ አይዋሰኝ፣
ከራማሽ አንቅሮ አሽቀልቁሎ ይድፋኝ፣

… ብቻ እድል ላግኝ፡፡

ደስታ ተከስተ
BDU Security Service

## ይድረስ ለእንቅልፌ

የሞት አለም ልምምድ፣
የመደሰታችን ምስጢር፡፡
የመደሰታችን ማዕድ
ራስን ብቻ ማዳመጫ
ወደ ጥልቁ አለም መወጣጫ፡፡
ሀሳብ መጣል ሀሳብ መቁረጥ የሌለበት
ሰላምና ፀጥታ የነገሰበት፡፡
ያ ውብ አለም የሚታይብሽ፣
ፍፁም ነፃነት የሚታወጅብሽ፣
ግርግር ጭንቀት የሌለብሽ፡፡
የመደሰታችን ሚስጢር፣
የፍላጐት ትርምስ ‘ሚሰክንብሽ፣
የምኞት አበባ ‘ሚደርቅብሽ፣
ደማቅ እውነትን በቅንነት የምንተነፍስብሽ፣
ቅድስና የሚገለፅብሽ፡፡
ውብና ድንቅ ጊዜ፣
የመደሰታችን ሚስጢር ጊዜያዊ ድንዛዜ፡፡
በእኛነት ውስጥ የምትኖሪ፣
ከፊል ሕይወትን ተጋሪ፡፡
የሞት ዓለም ልምምድ፣
አልፎ አልፎ የግለፍትወት መንገድ፣
ሞትና ሕያውነት ‘ሚታደምብሽ የጋራ ማዕድ፡፡
ሀብትነትን አዳህይተሽ፣
ልዩነትን ድርና ማግ ላደረግሽ፣
እኛነታችን  ውስጥ ያለሽ፣
ሰላማችንን እንዳበዛሽ ምስጋናችን ይድረስሽ፡፡

አትክልት ዳኛው
ከቢ/ኢ/የስነልቦና ባለሙያ

# <<ሳይቃጠል በቅጠል >>

በመክሊት ጋረደው ገብረወልድ (meklit.gebrewold@gmail.com)

በተቋማዊ መዋቅር የተዋቀሩ ትምህርት የሚሰጡባቸው ትምህርት ቤቶችም በየዘርፉ እናያለን፡፡ ዓለማችን በሁለንተናዊ ዕድገት መጥቃ እንድትጓዝ ምንዛሪ ሆኖ ያገለገለም የዕውቀት ምንጭ ነው፡፡ በፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፍ ለሚሠሩ ስራዎች መሠረት ሆኖ ያገለግላል፡፡ ዓለማችን አህጉራችን ብሎም ሀገራችን በየደረጃው የትምህርትን ተደራሽነት ለማሳደግ ከተለያዩ ሀገር በቀልና በተለያዩ ደረጃዎች ከተዋቀሩ ድርጅቶች ጋር እየተሰራ የሚገኝበት ወቅትም ነው፡፡

ባደጉና ትልልቅ በሆኑ የዓለማች ከተማዎች የሚገኝ አንድ ቤተሰብ እና ያላደጉ ብዙም ሰው የማይኖርባቸው አውራጃዎች የሚኖር ቤተሰብ ውስጥ የአረዳድና የመረጃ ደረጃቸው ቢለያይም ትምህርት የሰውን ልጅ ህይወት መለወጥ እንደሚችል አምነው በየአቅማቸው ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ሲልኳቸው አንዳች ለውጥ ሲፈጥር ለማየት ዕለት ተዕለት እንደወላጅ በየኑሮ ደረጃቸው ሲተጉ እናያለን፡፡በአንጻራዊ መልኩም ትምህርት ቤት ገብተው መማር እየፈለጉ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ትምህርት ቤት መግባት ያልቻሉ ትምህርት ቤት ገብተው ለመማር ያልታደሉ ሰዎችንም እናስተውላለን፡፡ ሌሎች ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች በተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች ያሉ እራሳቸውን እየደገፉ እየሰሩ የሚማሩ ጎበዝ ሰዎች እንዳሉ የብዙ ሰዎች ሕይወት ምስክር ነው፡፡ በዚሁ መጠን ደግሞ የጀመሩትን ትምህርት ሳይጨርሱ ጀምረው በተለያዩና በቀላሉ ቢደገፉ ማለፍ በሚያስችሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሲያቋርጡ ይስተዋላሉ፡፡

በዚህ ረገድ ከሌሎች የትምህርት ደረጃዎች በበለጠ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ደረጃ ለማመን በሚከብድ እና በተለየ መልኩ በጣም ሰፊ የሆኑ የተለያዩ ሁኔታዎችን እንመለከታለን፡፡ በእኛ ሀገር ደረጃ ከዚህ ሁኔታ ጋር በተገናኘ የምንሰማቸው እና የምናያቸው ደግሞ በርካታ ናቸው፡፡ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመሆን በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ከመነሻ ጀምሮ በመደገፍና በማበረታታት የጀመሩትን ትምህርት እንዲጨርሱ የበኩላቸውን በመወጣትና የተለያዩ ህጋዊ መዋቅርና የአሰራር መርህ ያላቸውን ማህበራትን፣ ሀገር-በቀል ድርጅቶችን፣ ዓለም ዓቀፍና ሌሎች ተቋማትን ለማበረታታት ዝግጁ ሆነው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ የሀገራችን ተቋማት መሃል ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አንዱ ሲሆን የተለያዩ የትምህርት ዘርፎችን ተደራሽነትንና ጥራትን ለማሳደግ እየሰራ ያለ ተቋም ለመሆኑ በምስራቅ አፍሪካ አንድ ሁለት ተብለው ሊዘረዘሩ የሚችሉ ስራዎቹ ምስክሮች ናቸው፡፡ በዚህ ሰፊ ተቋሙ ቦታ ተሰጥቷቸው ከሚሰራባቸው ማህበራዊ ስራዎች አንዱ ተማሪዎቹ ከትምህርት ገበታቸው ሊያፈናቅሏቸው የሚችሉ ችግሮች ለመፍታት የሚሰሩ አካላት መኖር ነው፡፡ እነዚህ አካላት እያንዳንዱን ተማሪ ለመድረስ ዕለት ዕለት እየሰሩ የሚገኙና ከሌሎች ማህበራትና ተቋማት ጋርም ለመስራት ዝግጁ ከመሆናቸውም ባሻገር የሚያበረታቱም ጭምር ናቸው፡፡ ለመሆኑ እነዚህ ማህበራትና ተቋማት ሊሰሩባቸው የሚችሉባቸው ጉዳዮች ምን ይሆኑ? በተለያዩ የስራ መስክ ተሰማርተው የሚገኙ ሰዎችና መምህራን (ለተማሪዎች ቅርብ በመሆናቸው ከሚያስተውሏቸውና ከራሳቸው ልምዶች) ምን ይላሉ?

አቶ ታደሰ ፈንታ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህር

በዩኒቨርሲቲዎች ላይ የሚማሩ አንዳንድ ተማሪዎች በተለያየ መልኩ አላማዎቻቸውን ሳያሳኩ ወደማይፈለጉ ነገሮች ይገባሉ፡፡ ለእነዚህና መሰል ጉዳዮች መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ደግሞ 1ኛ ተማሪዎች ስለመጡበት እና ወደፊት ስለሚሆኑት ነገር ራዕይ ይዘው መንቀሳቀስ ሲችሉ ከራሳቸው አልፈው ሌላውን መጥቀም የሚችሉበት ቦታ ላይ ይደርሳሉ፤ 2ኛ የሚያዩትንና ሰው የሆነውን ሳይሆን ያሉበትንና እራሳቸውን ሆነው መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ በዩኒቨርሲቲዎች ከተለያዩ አካባቢ የተውጣጡ ተማሪዎች ስለሆኑ የተለያየ ባህል እና አስተዳደግ ይዘው ስለሚመጡ ሌሎችን የመምሰልና እንደሌሎቹ ለመሆን ሲሞክሩ ችግር ይፈጠራል፤ 3ኛ ምንም እንኳን ወጣትነት ጊዜ ቢሆንም በወጣትነት መደረግ ያለበትን እና መደረግ የሌለበትን ነገሮች በአግባቡ ማገናዘብ መቻል ሌላው አላማቸውን ጠብቀው እንዲወጡ ያደርጋል፤ 4ኛ አንዳንድ ተማሪዎች ራሳቸውን ከሌሎች ያነሱና እንደ ሌሎቹ መሆን እንደማይችሉ አስቀድመው በማሰብ ራሳቸውን በራሳቸው አሳንሰው ሊሰሩ የሚገባቸውን ያክል ሳይሰሩ ይቀሩና ከሚፈልጉት ነገር መራቅ ይጀምራሉ፡፡ ከዛም ወዳልተፈለገ ነገር ያመሩና ህይወታቸውን ከዩኒቨርሲቲ ያላቅቃሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በግቢ ውስጥ የሚኖረን ጓደኛ እጅግ በጣም ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ በአካባቢም ሆነ በተለያዩ ነገሮች እኛን ከሚመስሉ ጋር መሆን እጅግ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በመጨረሻም በሀይማኖት ጠንካራ እንዲሆኑ ማድረግ ማለትም የሚከተሉት ሀይማኖትን በማጠንከር ለህይወታቸው ቦታ መስጠት ሲጀምሩ ነገሮች በቀላሉ ማስተካከል ይቻላል ብዬ አምናለሁ፡፡

አቶ ሞገስ ገብረእግዚአብሄር በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህብረተሰብ ሳይንስ ፋኩሊቲ መምህር



ሰው ሁሌ እየተለወጠ ነው የሚሄደው፡፡ ፖዘቲቭ ለውጥ ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ አንዳንዶቹ ከቁጥጥር ውጪ የሆኑ ናቸው እየከፋፈልን ማየት እንችላለን፡፡ አንዳንዶቹ ቁጭ ብለው ነው የሚጠብቁት፡፡ ህይወት ዕድል ነው፡፡ ህይወትን የምታዩበት መነጽር ወሳኝ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲ አዲስ አካባቢ ነው፤ ሰው ማህበራዊ ህይወትን የሚጀምርበት ነው፡፡ የተስፋም የውድቀትም ቦታ ነው፡፡ ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲ ከመግባታቸው በፊት የህይወት ክህሎት ትምህርት ማግኘት እንዲችሉ መርዳት ቢቻልና በየዲፓርትመንቱ በቅርብ ክትትል ቢኖር እላለሁ፡፡ በቂ ግን አይደለም፡፡ አካዳሚክ ብቻ ነው ትልቅ ተደርጎ የሚታየው ማማከር ላይ ስራ ቢሰራ፡፡ አባቴና እናቴ ተጣልተዋል ብሎ የሚሄድ ተማሪ ይኖራል፡፡ ተማሪ በተማሪ የማማከር ፕሮግራም ቢዘጋጅ፡፡ ኢኮኖሚካል ችግር በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ሶስት ዓመት ተደግፎ መማር እየቻለ ሲመለስ ይከብዳል፡፡ ራስ አገዝ የሆነ ማህበር ሲኖር ብድር እስከማግኘት የሚቻልበት አሰራር ሊፈጠር ይችላል፡፡ አንድ ካምፓኒ ሁለት ወይም ሶስት ተማሪዎችን መደገፍ/መርዳት ይችላል ግን ለዚህ ደግሞ መመቻቸት ያለባቸው ነገሮች መስተካከል አለባቸው፡፡ ድህነት በጣም የከፋ ችግር ነው፡፡ በገንዘብ ብቻ ሳይሆን የአመለካከት ችግርም አለ፡፡ አብሮ መኖርንና ማካፈልን ልምድ ብናደርግ በጋራ መሮጥ እንችላለን፡፡ አምስት ስድስት ሰዎች ሆኖ ከመሮጥ ሰዎችን ጨምሮ ሃያ ሆኖ መሮጡ የተሻለ ነው፡፡

ወ/ሪት ጥሩወርቅ ዘላለም በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የትምህርትና ስነባህርይ ሳይንስ ፋኩልቲ መምህርት



ትምህርት የሰውን ህይወት ይለውጣል፡፡ በተማረው ትምህርት መቀየር አለበት፡፡ አንድ ተማሪ አንድ ህልም ይኖረዋል፡፡ ለምን እንደመጡ የማያውቁ ጥቂት ተማሪዎች ይኖራሉ፡፡ ችግሮች ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ የቋንቋ ችግር (በሽታቸውን በአማርኛ ማስረዳት አቅቷቸው የሚቸገሩ አሉ)፤ የዩኒቨርሲቲን ህይወት አለመልመድ፤ በፕሮግራም መንቀሳቀስ የሚከብዳቸው ተማሪዎች መኖር፤ በቤተሰብ ቁጥጥር ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ተማሪዎች እዚህ ሲመጡ ግራ መጋባትና ውሳኔ የመስጠት ችግር ይታይባቸዋል፡፡ የህይወት ክህሎት ስልጠና መሰጠት ተጀምሯል፡፡ ነገር ግን በቂ አይደለም፡፡ ምኑን ከምን ላድርገው ለሚል ተማሪ የሁለት የሶስት ቀን ስልጠና በቂ አይደለም፡፡ የገንዘብ ችግርም ይኖራል፡፡ ከቤተሰብ ምንም የማይላክላቸው ተማሪዎች አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ እየሰሩ ቤተሰብ የሚደግፉ አሉ፡፡ ፋን (Female Academician Network) የሴት መምህራን ቡድን ለምሳሌ በጋራ የሚረዷቸው ተማሪዎች አሉ፡፡ የተማሪ ህብረት፤ ቪዥን ፎር አካዳሚ እና የስርዓተ ጾታ ጽ/ቤት በዚህ ዙሪያ ይሰራሉ፡፡ ልጅ ይዘው የሚንከራተቱም አሉ፡፡ በዚህ አጋጣሚ መምህራንን ለማመስገን እወዳለሁ፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚማሩ ሁለት ሴት ተማሪዎችን ለመርዳት ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል፡፡ ስርዓተ ጾታ ቢሮ እሰራ ነበር ብዙ ተማሪዎች ይመጣሉ እና ጸ/ቤቱን በራሴ ችግር ስለቅ ተማሪዎቹ እኔን ፍለጋ ይመጣሉ፡፡ ልጅ ይዛ እያየሁኝ ወተት እያጣ እያየሁኝ ልለፍ ብል ሰላም አላገኝም፡፡ የአንዲት ሴት ተማሪ ሁኔታ ግን መምህራንን በማስተባበር እንድትረዳ ለመስራት እንድነሳ አድርጎኛል በዚህ አጋጣሚ መምህርት ፀጋነሽን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ ከባለፈው ዓመት ጀምሮ አንቺ በዋናው ግቢ እንዲቋቋም ስትሰሪበት የነበረው የሴት ተማሪዎች እራስ-አገዝ ቡድን አንድ አንድ ብር በወር በቡድኑ በኩል ተሰብስቦ የከፋ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች እንዲውል መስጠት እንችላለን ብለው ለአባልነት የተመዘገቡ ሴት ተማሪዎች ከሶስት መቶ በላይ ናቸው፡፡ ይህም ጅማሮ የሴት ተማሪዎች ራዝ-አገዝ ቡድን ሆኖ ሴት ተማሪዎችን በማሳተፍ ጀምሮ ወንድ ተማሪዎችንም ተሳታፊና ተደራሽ እንዲሆኑ ውጥን የያዘ ጭምር ነበር፡፡ ይህን ቡድን ስራ ሲሰራ ለማየት ግን ተማሪ ህብረት ላይ ህጋዊ እውቅና ማግኘት አስቸጋሪ ሆኖ ነው ያገኘነው፡፡በዚህ አጋጣሚ በዚህ መልኩ ቢሆን የሚለን አካል ቢገኝ ደስ ይለናል፡፡ ልምድ ያላቸው ልምዳቸውን ሊያካፍሉን ይችላሉ፡፡በመጨረሻም ትምህርት እንዳልሽው ሀብት ነው፡፡ እውቀት በማጣታቸው ቆራጥነት በማጣት የሚንዘላዘሉ አሉ፡፡ ማህበራዊ ችግሮች የሚገጥሟቸው ተማሪዎችም አሉ፡፡ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያለ ህይወት ዋጋ የሚያስከፍል ነው፡፡የሆነ አይነት ነገር ቢቋቋም ለሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች መማሪያ ይሆናል፡፡ አንድ ተማሪ ስንሰጠው ገንዘብ ብቻ ሳይሆን አደራም ጭምር ነው የምንሰጠው፡፡ ሁሉን አድርገሽ ደግሞ አትችዪውም ተነሳሽነት ያላቸው ድርጅቶች/አካላት ቢያግዙንና



ግዮን አለምሰገድ በሙሉዓለም የባህል ማዕከል የትወና ባለሙያ

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ